


# ትንሣኤ



«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፤ ሥርዓትና ዜና፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብህ

ም አዘጋጅ መ ክንፈ
ርግብ ማርቆስ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

## አርእስት — ገጽ

ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእሰ አንቀጽ ገበሬ ዘርን ሊዘራ ወጣ ........ ፪
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዜና ዕረፍት
ከፀሐተ ነፍስ እስከ ወረደ መቃብር ........ ፬
ታማኝ አገልጋይ ........ ፲፪
አንድነትና ሦስትነት በአብረሃም ቤት ........ ፲፬
ዜና ሊቃውንት (የብፁዕ አቡነ አብረሃም አጭር የሕይወት ታሪክ) ........ ፲፮
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጥቅሶች ........ ፲፯
ዜና ዕረፍት (የሊቀ መንክራት በርክ) ........ ፳
ስለቅዱስነታቸው የነዘን መግለጫ ........ ፳፩
አፍና ልብ በአንድ ላይ ይመኑ ........ ፳፪
ቅዱስ ዑራኤል መራሔ ብርሃናት ........ ፳፫
የደስታ ዋስትና ምን ይሆን ? ........ ፳፬




ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፡

በመጀመሪያ ሰላም ለሁላችሁ የሚለውን ሰላምታ ለእናንተ መንፈሳውያን ወንድሞቼ በትሕትና አቀርባለሁ ፡

በአማርኛና በእንግሊዝኛ እየታተሙ የሚወጡትን መጽሔቶቻችሁንና ጋዜጦቻችሁን ተከታትዬ የማነብና በእንጻሩም ከፍተኛ ትምህርትን የቀሰምኩባቸው መሆኑን ስገልጽ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ ፡ ዛሬ ለጽሑፍ ተሳታፊነት ብቅ ያሰኘኝ ከዚህ በታች የዘረዘርኳቸውን ጥያቄዎች ለማቅረብና ትክክለኛ መልስ ከእናንተ ለማግኘት ስለሆነ እነሡም በዛም ቀለለም ሳትሉ ትምህርቱን ትሰጡኝ ዘንድ በትሕትና እጠይቃለሁ ።

፩ኛ/ በእንግሊዝኛ ታትሞ የወጣው ትንሣኤ ጋዜጣችሁ መስከረም ፲፱፻፹ ዓ.ም በገጽ ፪ ላይ የቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) ትውልድ ሶርያ ነው ይላል ከሌላ መጽሐፍ እንዳገኘሁት .. መቶ ተለመደና ከተከላ ዝምድና .. ከሚለው መጽሐፍ ገጽ ፹፩ ላይ የፍሬምናጦስ ትውልድ ግሪክ ነው ይላል ደግሞ ከሌላ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሚለው መጽሐፍ በገጽ ፳፬ ላይ ፍሬምናጦስ ትውልዱ ሶርያ ነው ይለዋል ። እንግዲህ ከዚህ በመነሣት ትክክለኛውን ትገልጹልኝ ዘንድ በትሕትና እጠይቃለሁ ፡

፪ኛ/ ሥረወ ሃይማኖት በተባለው መጽሐፍ በገጽ ፩፻፳፮ ላይ ተጽፎ እንዳገኘሁት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋውንና የደሙን ምሥጢር ለሐዋርያት የገለጸው ሐሙስ ማታ ከመስቀሉ በፊት ከአልዓዛር ቤት ነው ይላል ሆኖም የራት ግብዣው ከመደረጉ በፊት ክርስቶስ ስፍራውን ገልጦ የቤቱን ባለቤት ስም አልገለጸላቸውም ይህ ከሆነ ታዲያ ከአልዓዛር ቤት የተባለበትን ማስረጃ ብትገልጹልኝ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ ፡

የመንፈስ ቅዱስ ወንድማችሁ
ሻለቃ ሙሉሸዋ ጋረዶ

<u>መልስ</u> ሻለቃ ሙሉሸዋ ጋረዶ ስለአቀረቡልን ሰላምታ አጸፋውን እየሰጠን ላቀረቧቸው ጥያቄዎች መልሶቻቸውን ቀጥለን እናቀርባለን ።

ጠያቂው በመጀመሪያ ያቀረቡት የአባ ሰላማ ሀገሩ የት እንደ ሆነ እርግጠኛውን እንድናስረዳዎ ነው አባ ሰላማ ሀገሩ ያለ ጥርጥር ግሪክ ነው ። አንዳንድ ጸሐፊዎች ሀገሩ ሶሪያ ነው ጢሮስ ነው እያሉ የሚጽፉት ከግሪክ ወደ ሶርያ በመሄድ የኖረውን ዘመን በመመልከት ነው እንጂ የአባ ሰላማ ሀገር ግሪክ ነው ይህንን መልስ የሰጠነው የታሪክ መጻሕፍትን ተመልክተን ሊቃውንት ጠይቀን በሚገባ አጣርተን ነውና ሻለቃ ሙሉሸዋ አይጠራጠሩ ።

በተጨማሪም ሐምሌ ፳፯ የሚነበበውን ስንክሣርና የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ — አክሱም — ዛጉዬ — ይመልከቱ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሊያገኙ ይችላሉ ገጽ ፫፻፯ በታሪክ ነገሥትም ግሪካዊ መሆኑ ተጽፏል ።

በሁለተኛው ጥያቄዎ ደግሞ ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ዓርብ ሊሰቀል ሐሙስ ማታ የራት ግብዣ አድርጐ የሥጋውንና የደሙን ምሥጢር ለሐዋርያት ያሳያቸው በአልዓዛር ቤት መሆኑን የሚያስረዳ መጽሐፍ እንድንነግረዎና እንድናስረዳዎ ጠይቀውናል። የዚህኑ መልስ ለመረዳት በሰፊው ከፈለጉ በ፩ወር አንድ ጊዜ በአንድ ዓመት ፫ ጊዜ ታትሞ ከሚወጣው ማዕዶት መጽሔታችን ሚያዝያ ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ቁጥር ፳፫ ከገጽ ፲፮—፲፯ ጸሎተ ሐሙስ በጽርሐ ኒቆዲሞስ በሚል ርእስ የተጻፈውን ይመልከቱ መጽሔቱ የለኝም እንዳይሉ የመጽሔቶቻችንና የጋዜጦቻችን ደንበኛችን መሆንዎን በጥያቄዎ ላይ ገልጸውልናል ።

ቢሆንም በአጭሩ እንግለጽልዎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ሥጋውንና ደሙን ለሐዋርያት ያሳያቸው በአልዓዛር ቤት በኒቆዲሞስ አዳራሽ በለምጻሙ በስምዖን ቤትም ይላል ፩ኛ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ተቀመጠ ይላል ፪ኛ. የአልዓዛር ቤት መሆኑን የሚያመለክት ማርቆስ ፲፬.፲፪—፲፯ ሉቃስ ፳፪.፯—፲፬ የተጻፈው ቃል ነው ፡

(ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ገበሬ ዘርን ሊዘራ ወጣ

በሀገራችን በአንድ ዓመት ውስጥ አራት የተለያዩ ወቅቶች አሉ እነርሱም ክረምት መፀው ኀጋይ ፀደይ ሚባሉት ናቸው ለእነዚህም ወቅቶች የተለያዩ ጠባዮች አሏቸው ለምሳሌ ክረምት የዘር ወቅት ሲሆን ደመና ጉም ዝናብ ነጐድጓድ ጉርፍ ማዕበል ብርድና የመሳሰሉት የሚጠነክሩበት ነው አዝርዕት ተዘርተው የሚበቅሉበት አትክልት ተተክተው የሚጸድቁበት መሬት በቡቃያና በአረንጓዴ ቅጠል ተሸፍና የምትታይበትም በዚሁ ወቅት ነው ፡

መፀው ደግሞ የነፋስ የአበባ የፍሬ ወቅት ሲሆን ኀጋይ የፀሐይ ጊዜ ነው እንዲሁም ፀደይ የበልግ ወቅት ነው ከላይ እንደተገለጸው ለእያንዳንዱ ክፍለ ዘመን የተለያየ ጠባይ አለው የሁሉንም ጠባይ ተንትኖ ለመጻፍ ሰፋ ያለ ዓምድን ይጠይቃል ስለዚህ የቀሩትን ለሌላ ጊዜ ሰቆይተን ስለዘመነ ክረምቱ ብቻ እንመለከታለን ክረምት የሚጀምረው ሰኔ ፳፭ ቀን ሆኖ ማለቂያው መስከረም ፳፭ ቀን ነው ፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሁኖ ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ተወልዶ ያስተምርበት በነበረው ዘመን ብዙ ትምህርቶችን በምሳሌ አስተምሯል ካስተማረባቸውም ምሳሌዎች አንዱን ቀጥለን እንመለከታለን ፡

"እነሆ ገበሬ ዘርን ሊዘራ ወጣ ሲዘራም አነዳንዱ በመንገድ ላይ ወደቀ ወፎችም መጥተው ለቀሙው በሉት ሌላው ብዙ መሬት በሌለው ጭንጫ ላይ ወደቀ ጥልቅ መሬት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ ፤ ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ እሾህም ወጣና አነቀው ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ አንዱም ቀንጣት መቶ ስልሳ ፡ ሰላሳ ፍሬን አፈራ ይልና የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ" በማለት ያበቃል ማቴ.፲፫.፩ – ፱

ይህንን ትምህርታዊ ምሳሌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያን ዘመን ቢያስተምረውም በዚያው ተውስኖ የቀረ ትምህርት አይደለም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የተነሡትን ምእመናን ሲያስተምር ኑሯል አሁንም ያስተምራል ይመክራል ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚነሡትን ምእመናን ይመክራል ያስተምራል ፡

በገበሬ የተመሰለው ክርስቶስ ሲሆን ዘሩ የሚያስተምረው ቃል መሬቱ የምእመናን ልቡና መሆኑ ታውቋል አሁን በክርስቶስ እግር የተተኩ መምህራን ናቸው ብዙ አስተማሪዎች በሚያስተምሩበት ጊዜ የሚነገረውን ቃል ምእመናኑ ያዳምጣሉ ነገር ግን ካዳመጡ በኋላ የሰሙትን ቃል ሁሉ ከሥራ ላይ አንዳያውሉት ፡ ከፈጣሪያቸው ጋር የሚያገናኝ የጽድቅ ሥራም እንዳይሠሩ ጸላዕያነ ሠናያት አጋንንት ኃይላቸውን አጠንክረው ይዋጓቸዋል ፡

በጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ፈጥኖ በቅሎ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ተንሽ ሳይቆይ ጠውልጎ ደርቆ ድራሹ እንደጠፋ አንዳንድ ምእመናንም ትንሽ ችግር በደርሰባቸው ጊዜ የደረሰባቸውን ችግር በትዕግሥት ለማሳለፍ አይችሉም ጥቂት ሳይቆዩ ፈጣሪያቸውን ይክዳሉ ሃይማኖታቸውንም ይለውጣሉ ሌላው ምሳሌ በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ነው በበቀለ ጊዜ እሾሁ አስጨንቆ ይዞ ያለ ፍሬ እንዳስቀረው የዚህ ዓለም ባለጸጉችም የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ ያለዋጋ የሚያስቀሩት ለታላይ ሀብት ስለ ሥልጣን በማይገባ መንገድ ማሰብ ፥ የሴት መውደድ ፥ የልጆች ፍቅርና በጠቀላላ በዓለም ላይ የሚገኘውን ማፍቀር ናቸው ።

በመጨረሻ የተነገረው በመልካም መሬት ላይ ተዘርቶ አንዱ ቀንጣት መቶ ስልሳ ሰላሣ ፍሬ ያፈራው ዘር ነው ። በዚህ በጥሩ መሬት ላይ በወደቀው ዘር የተመሰሉት የሰሙትን ቃል



እግዚአብሔር ወዲያና ወዲህ ሳይሉ በቀጥታ በሥራ ላይ ለማዋል የሚችሉ ምእመናን ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሉም ለመልካም ሥራ ቢሰለፉም በተግባራቸው አንድ ዓይነት ዋጋን አያገኙም ለሩጫ ውድድር የገቡ ሁሉ መበላለጥ እንዳለባቸው በዓለም ላይ ለተወሰነ ጊዜ እንዲኖሩ የተፈጠሩ ሰዎችም በሚሠሩት መልካም ሥራ ከክርስቶስ የሚያገኙት ክብር የተለያየ ነው ።

ይህንንም መተርጉማነ መጻሕፍት ሊቃውንት ሲያብራሩ ባለ መቶ ፍሬ የተባሉ መልካም ሥራ ሠርተው ከፍጹምነት የደረሱ ሲሆኑ ባለስልሳ ከማዕከላዊነት የደረሱ ናቸው ። ባለሰላሣ የተባሉ ደግሞ ገና በወጣኒነት ደረጃ የሚገኙ ናቸው ይላሉ ። ምሳሌው መንፈሳዊ ትምህርትን ብቻ ይዞ የሚተረጉም ሳይሆን ሥጋዊ ሥራንም የሚያሳስብ ነው በዚህ ዓለም ጠንክሮ ካልሠሩ ካልወጡ ካልወረዱ ብልፅግና ሊገኝ አይችልም ።

ማንኛውም ሰው አካል በዘየአክል እያለው ማረስ መቆፈር መውጣት መውረድ አለበት እንጂ መስነፍ አይኖርበትም ጠንካራው ታታሪ ገበሬ ባለመቶ መካከለኛው ባለ ስሳ ዝቅተኛው ባለ ሰላሣ ለመሆን ይችላል ፡

ጠቢቡ ሰሎሞን ምድሩን የሚያርስ እንጀራን ይጠግባል ሲል እንደተናገረው ራስን ችሎ ለሌላውም ለመትረፍ በዘመነ ክረምት ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል አሁን ክረምት ነው ወቅቱም የዝናም ወቅት መሆኑ አያጠያይቅም ገበሬው የተበጠረውን የተንጠረጠረውን ንጹሕ ዘር ከጐተራው ከሪቁ አውጥቶ ሳይጠራጠር ለመሬት ያበድራል መሬትም ገበሬው የሰጣትን አደራ ተቀብላ በመከር ወቅት በወርኀ መፀው ማለት ነው ከእነ ወለዱ ለገበሬው ታስረክበዋለች ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሲገልጽ ..ብዙ ጊዜ በእርሷ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት ለሚያርሷትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና .. ይላል ዕብ.፮.፯ ይኸው ሐዋርያ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ መንጋውን እየጠበቀ ወተቱን የማይጠጣ ማነው? ብሎ እንደተናገረው በክረምት ካላረሱ ካልቆፈሩ ካልዘሩና ካልተከሉ በመከር ጊዜ እሸት ቆርጦ ለመብላት አይቻልም መንጋንም በንቃትና በትጋት ካልጠበቁ ወተትን አልቦ ለመጠጣት አይቻልም ።

ስለዚህ በዚህ ወቅት በይበልጥ በግብርና ሥራ የተሠማሩ ገበሬዎች ብርዱን ዝናቡን ጭቃውን ሳይሰቀቁ ተግተውና ነቅተው የመሥራት ግዴታ እንዳለባቸው ሊገነዘቡት ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ዜና ዕረፍት

## ከፀዓተ ነፍስ እስከ ወሪደ መቃብር

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከቅርብ ቀን ወዲህ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

የቅዱስነታቸው ዜና ዕረፍት እንደተሰማ ፡—

፩ኛ/ የቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ካህናትና የሰንበት ተማሮች

፪ኛ/ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካህናትና የሰንበት ተማሮች

፫ኛ/ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካህናትና የሰንበት ተማሮች


፬ኛ/ የታዕካ ነገሥት በዓታ ካህናትና የሰንበት ተማሮች

፭ኛ/ የመ/መ/ቅዱስ ገብርኤል ካህናትና የሰንበት ተማሮች

የእነዚሁ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች በመንበረ ፓትርያርክ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተሰበሰቡ ፡ በዚያም እንደተሰበሰቡ በመጋቢ ካህናት አማካይነት የቅዱስነታቸው አስከሬን ወደ አለበት ሲሄዱ በሰልፍ መጓዝ እንዳለባቸውና የሰልፉም ቅደም ተከተል ተገለጸላቸው ፡ እነርሱም በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት በቅደም ተከተል ሆነው በሰልፍ የቅዱስነታቸው አስከሬን ወደ አረፈበት ሄደው ኃዘናቸውን እየገለጹ በተወሰነላቸው ስፍራ ቆሙ ።

ልክ ከቀኑ ፲፪ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ሲሆን የቅዱስነታቸው አስከሬን አርፎ ከነበረበት ስፍራ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታጅቦ ከአስከሬን ተሸካሚው መኪና ውስጥ ገባና ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ለመጓዝ ሊጀምር ሲል የሰልፉ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነበር ።

ከላይ ስማቸው የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ፡ የሰንበት



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስነታቸውን አስከሬን ተሸክመው ከመንበረ ፓትርያርክ ሲወጡ

ተማሮች ፡ ዩኒፎርም ለብሰው የመስቀል ምልክት ዓርማ በፊት ለፊት ያለበት ቆብ ደፍተው አስከሬኑ በሚያልፍበት መንገድ ግራና ቀኝ ፡ ቀጥሎ የቅዱስ ጳውሎስ ከ/መ/ት/ተማሮች ፡ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን ተሰለፉ ።

እንዲሁም ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ባለመጾር መስቀል የያዙ ዲያቆናት በቅዱስነታቸው አስከሬን በስተኋላ ከእነርሱ ቀጥለው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ጽንሐሕና የእጅ መስቀል የያዙ ቀሳውስት ተሰልፈዋል ።

ቀጥሎ ጥቋቁር ልብስ የለበሱ ፬ መነኮሳት የቅዱስነታቸውን የክብር ዕቃዎች ይዘው በአስከሬኑ በስተኋላ ሲሰለፉ በእነርሱ ግራና ቀኝ ደግሞ በጥቁር መደብ ሆኖ በወርቅ የተዘመዘመ ሞጣሕት ለብሰው የወርቅ ባለመጾር መስቀል የያዙ ፮ ዲያቆናት ሦስቱ በቀኝ ሦስቱ በግራ ሆነው ቆሙ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በቅዱስነታቸው አስከሬን በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ቁመው መሪር የሆነ ኃዘናቸውን በመግለጽ እንባቸውን ያፈሱት ጀመር።

በዚሁ ሁኔታ ጉዞው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን አመራ በጉዞውም ላይ መዘምራኑ "አሌፍ ብፁዓን እለ ንጹሐን በፍኖቶሙ" እያሉ እየዘመሩ ፡ የሰንበት ተማሮችም ከፍ ባለ መዝሙራዊ ድምፅ ኃዘናቸውን እየገለጹ ቅዱስነታቸው ከራሳቸው ደመወዝ ወጭ በማድረግ እያበሉ፡ እያጠጡ እያለበሱ እያስተማሩ የሚያሳድጓቸው ዕጓለ ማውታ ሕፃናት ኃዘናቸው አልገታም ብሏቸው እየወደቁ እየተነሡ እየጮሁ በማልቀስ የቅዱስነታቸው አስከሬን ከምሽቱ ፩ ሰዓት ከ፴ የቂቃ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ አርፏል ።

ከዚያም በኋላ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት መሪነት ጸሎተ ምህላ ፡ ደርሶ ኃዘንተኛው ወደ እየቤቱ ሄደ፡ል በዚህም ሌሊት አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ፹፮ አድባራትና ገዳማት ጸሎተ ሰዓታትና ማኅ



የቅዱስነታቸው አስከሬን በእጀብ ወደመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲጓዝ

ሌት ሲደርስ አድሯል ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትም የቅዱስነታቸው አስከሬን ባረፈበት በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲጸልዩ አድረዋል ።

ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ከጧቱ ፩ ሰዓት ጀምሮ የአዲስ አበባ ከተማ ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት ዩኒፎርም የለበሱ የሰንበት ተማሮች የቅዱስ ጳውሎስ ከ/መ/ትምህርት ቤት ተማሮች በሰበታ ደናግል ጠባባት ገዳም የሚኖሩ መነኮሳይያት በዚያው ገዳም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እየተረዱ የሚያድጉ እጓለ ማውታ ሕፃናት ምእመናንና ምእመናት የቅዱስነታቸው አስከሬን አርፎ ወደ አደረበት ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ኃዘናቸውን መግለጽ ቀጥለዋል ።

ከጧቱ በሁለት ሰዓት ላይ ጸሎተ ኪዳን በሊቃነ ጳጳሳቱ መሪነት በአማርኛ ከተጸለየ በኋላ በእንተ እለ ኖሙ ሲደርስ ዘፃመወ በዓለም የሐዩ ለዝሉፉ

— እስመ ኢይሬእዩ ሙስና

ሶበ ትሬእዮሙ ለጠቢባን

ይመውቱ የሚለው መዝሙረ ዳዊት ተሰብኮ ሲያበቃ የማቴ. ወንጌል ምዕ.፳፭ ፡፲፬—፴ ያለው በአቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተነበበ ፡ ጸሎተ ፍትሐቱ ሲፈጸም የቅዱስ ጳውሎስ ከ/መ/ት/ተማሮች በኅብረት "ብፁዕ አባ ተክለ ሃይማኖት ዘእምን ዕሱ ሕይወቱ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ከመ አብ ዘኮነ ለእጓለ ማውታ ፈጻሚ ተጽናሶን ለዕቤራት እስመ ውስተ ልብሱ ክህነትእስመ ውስተ ልብሱ ክህነተ

፭


www.ethiopianorthodox.org

ኩሉ ዓለም" የሚለውን እስመ ለዓለምና "ይቤልዎ ሕዝብ ለአባ ተክለ ሃይማኖት አይቴ ተሐውር ኅዲገከ ሀገረከ ዘአስተባዛኅከ በጸሎትከ ፡ ወይቤሎሙ ኢየኅድገክሙ እምዕለ ለክሙ ኅበወልድ ዘመጽአ እምዘርአ ዳዊት ዘስሙ አማኑኤል የሚለውን ዋይዜማ በቁም ዜማ ሦስት ሦስት ጊዜ በመዝለቅ የተሰማቸውን ኃዘን ገልፀዋል ።

፫ ሰዓት ከ፲፰ ደቂቃ ሲሆን በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት ተፈጽሞ ወደመንበረ ፀባዮት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለመጓዝ የሰልፍ ዝግጅትና የጉዞው ቅደም ተከተል በሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የትንሣኤ ዘጉባኤ አሳታሚ ድርጅት ሐላፊ ገለጻ ተደረገ ።

በተሰጠው መመሪያ መሠረት ሁሉም የተመደበላቸውን ቦታ ይዘው እንደተዘጋጁ ለ፬ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን በክንዳቸው ላይ የኀዘን ምልክት ጥቁር ካኪ አድርገው ጠብመንጃ የያዙና የሙዚቃ መሣሪያ ያነገቡ የክብር ዘበኞች መጥተው በዓውደ ምህረቱ ዙሪያ በሁለት በሁለት ረድፍ እየሆኑ ተሰለፉ ።

ወዲያውም ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የተውጣጡ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን ልብሰ ተክሆና ለብሰው ጽንሐሕ የያዙ ቀሳውስት ፡ ባለመጸር መስቀልና ጃንጥላ የያዙ ዲያቆናት ዩኒፎርም የለበሱ የሰንበት ተማሮች የቅዱስ ጳውሎስ ከ.መ.ት/ቤት ተማሮች በዓውደ ምሕረቱ ግራና ቀኝ ተሰልፈው የቅዱስነታቸውን አስከሬን መውጣት



ሊቀ ማዕምራን ደምፀ ገብረ መድኅን ለሰልፈኛው መመሪያ ሲሰጡ

ይጠባበቁ ጀመር ።

፬ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ሲሆን በልብሰ ተክህኖው ላይ መደቡ ጥቁር ሆኖ በወርቅ የተመኳሸ ሞጣህት ለብሰው የወርቅ መስቀል በመጸር የያዙ ፲ ዲያቆናት



የቅዱስነታቸውን አስከሬን አጅቦ ይጓዝ ከነበረው ሕዝበ ክርስቲያን በከፊል

በፊት ለፊት እየመሩ ፬ መነኮሳት ጥቋቁር ልብስና ቆብ ደፍተው የቅዱስነታቸውን የክብር ዕቃ ይዘው እየተከተሉ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታጅቦ የቅዱስነታቸው አስከሬን ወደ ዓውደ ምህረቱ ብቅ ባለ ጊዜ ግራ ቀኝ የተሰለፈው የክብር ዘብ በብረት ሰላምታ አቀረበ የክብር ዘብ ሙዚቀኞችም የኃዘን ማርሽ አሰሙ ። የአብያተ ክርስቲያናትም ደወሎች ለ፳ ደቂቃ ድምፃቸውን አሰሙ ።

ከዚህ በኋላ የቅዱስነታቸው አስከሬን በተዘጋጀለት ሠረገላ




ላይ ወጣ የቅዱስነታቸው አስከሬን ከአንገቱ በላይ የክብር አክሊሉን ደፍቶ በግልጽ ይታይ ስለነበር አስከሬኑን ስሞ ተሳልሞ ለመሰናበት አመቺ ነበር ።

አስከሬኑ በሰረገላው ላይ ከወጣ በኋላ ጉዞው ወደ መንበረ ፀባዮት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲያመራ የሰልፉ ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር ።

፩ኛ/ አስከሬኑ በሚያልፍበት መንገድ በስተግራ ዩኒፎርም የለበሱ የሰንበት ተማሮች ፡

፪ኛ/ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን በመንገዱ በስተቀኝ ቀጥሎ የሰዋስወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ ከ/መ/ት ተማሮች በሰበታ ደናግል ጠባባት ገዳም የሚኖሩ መነኮሳይያት እንዲሁም በዚያው ገዳም በሕፃናት ማሳደጊያ የሚገኙ ዕጓለ ማውታ ሕፃናት አብረው ተሰለፉ ከእነርሱ ቀጥለው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ባለመጸር መስቀልና ጃንጥላ የያዙ ዲያቆናት የወርቅና የብር ጽንሐሕ የያዙ ቀሳውስት አክሊል በራሳቸው ላይ ደፍተው ይከተላሉ በመንገዱም መካከል ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መደቡ ባለ ጥቁር ሆኖ ዳርና ዳሩ በወርቅ የተከፈፈ ሞጣህት የደረቡ ፲ ዲያቆናት የወርቅ መስቀል ይዘው ሲመሩ የቅዱስነታቸውን የክብር ዕቃ የያዙ ፬ መነኮሳት በሰልፍ ሆነው ይከተላሉ ቀጥሎም የቅዱስነታቸውን አስከሬን የያዘው ሠረገላ ሲጓዝ በፊት ለፊት ጥቋቁር ቀሚስ ለብሰው ጥቋቁር ካባ የደረቡ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ይመራሉ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አስከሬኑን በፊት በኋላ በቀኝ በግራ አጅበው ሲከተሉ የክብር ዘቡም ከቅዱስነታቸው አስከሬን በ፰ ሜትር ርቀት ሆኖ በማጀብ በቀስታ ይራመዳል የክብር ዘብ ሙዚቀኞችም የኃዘን ማርሽ ያሰማሉ ክቡራን ሚኒስትሮችም የቅዱስነታቸውን አስከሬን በክብር አጅበው በእግራቸው ይጓዛሉ በዚህ አኳኋን የቅዱስነታቸው አስከሬን ተጉዞ ለ፲ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን መንበረ ፀባዮት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በደረሰ ጊዜ የአብያተ ክርስቲያናት ደወሎች ድምፃቸው ለ፲ ደቂቃ አስተጋብቷል የቅዱስነታቸው አስከሬን ከካቴድራሉ ውስጥ ገብቶ በተዘጋጀለት ቦታ ከአረፈ በኋላ በ፲ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሯል የተቀደሰውም በ፫ መናብርት ሲሆን ጸሎተ ቅዳሴው የተመራው በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ነበር ።

ጸሎተ ቅዳሴውን ከመሩት



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የጠ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለቅዱስነታቸው የተሰማቸውን ኀዘን ይገልጻሉ



የቅዱስነታቸው አስከሬን መንበረ ፀባዮት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እንደደረሰ



www.ethiopianorthodox.org

ሊቃነ ጳጳሳት ጥቂቶቹ

፩. ብፁዕ አቡነ አብርሃም የመ/ፓትርያርክ ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳስ
፪. ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎ/ሀ/ሊቀ ጳጳስ
፫. ብፁዕ አቡነ ማትያስ የኢሉባቦር ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ
፬. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የከፋ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ
፭. ብፁዕ አቡነ ገሪማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሱዳን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ መምሪያ ተ/ዋና ጸሐፊ
፮. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የወሎ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ናቸው ።

በቅዳሴ ጊዜ የተሰበከው መዝሙረ ዳዊት ጽዋዓ ሕይወት እትሜጦ ወስመ እግዚአብሔር እጼውዕ ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር የሚለው ነው የተነበበው የማቴ. ወንጌል ፲፰ ፡ ፲፪ – ፲፬ ያለው ቃል ሲሆን ያነበቡትም ብፁዕ አቡነ አብርሃም የመንበረ ፓትርያርክ ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳስ ናቸው ከቅዳሴም በኋላ አበባ የማኖሩ ሥነ ሥርዓት የሚቀጥል መሆኑ ተገለጸ በቅዱስነታቸው የኀዘን መግለጫ ከመንግሥታውያንና ከሕዝባውያን ድርጅቶች እንዲሁም ከውጭ ሀገር የሃይማኖት ድርጅቶችና ከግለሰቦች የተቀመጡት አበባዎች ቁጥር ከ፩፻፲፫ በላይ መሆኑ ታውቋል ።

<u>ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም</u> ከሌሊቱ ፫ ሰዓት ጀምሮ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙት ፵፮ አድባራትና ገዳማት ጸሎተ ሰዓታትና ማኅሌት ተቁሞ አድሯል ።

ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘመምራን ዩኒፎርም የለበሱ የሰንበት ተማሮች እንዲሁም ምእመናንና ምእመናት የቅዱስ ፓትርያርኩ አስከሬን ወደአረፈበት መንበረ ፀባዖት ከሣጥኑ ውስጥ ተጋድሞ ከአንገቱ በላይ ፊቱ ግልጽ ሆኖ የመዓረግ ቆቡን (አክሊሉን) በራሱ ላይ እንደደፋ ከፍ ባለ ጠረጴዛ ላይ ሆኖ በስተውስጥ ትራስ ተደረጉለት በጠረጴዛ ላይ ስለተቀመጠ ለሁ




የቅዱስነታቸው አስከሬን ይህን ይመስል ነበር

ሉም በግለጽ ስለሚታይ ከላይ እንደተገለጸው ስሞ ተሳልሞ እጅ ነሥቶ ለመሰናበት አመቺ ነበር ።

በአስከሬኑ ዙሪያ አበባዎች ተቀምጠዋል ፡ በፊት ለፊቱም ቅድስት ሥላሴ እየመጡ የተሰማቸውን ኃዘን በመግለጽ የተመደበላቸውን ስፍራ መያዝ ጀምረዋል።

የቅዱስነታቸውም አስከሬን አቀማመጥ እንደዚህ ነበር አስከሬኑ



በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በቅዱስነታቸው አስከሬን አጠገብ ቆመው ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱ



በጥቋቁር ልብስ በተሸፈነ ጠረጴዛ ላይ የቅዱስነታቸው የክብር ዕቃዎች ተደርድረው ይታያሉ በመጠነኛ ቁመት የተነማ የቅዱስነታቸው ፎቶ ከፍ ባለ ጠረጴዛ ላይ ከበስተኋላው ሰላድው ተደግፎ ቁሟል በፎቶው በስተቀኝ ሁለት መነኮሳት በስተግራ ሁለት መነኮሳት ካባ ላንቃ ለብሰው ባለመጾር መስቀል ይዘው ቁመዋል ፡ በእነርሱ በስተኋላ ጥቋቁር ሞጣህት የለበሱ ፮ ዲያቆናት መስቀል ይዘው በሰልፍ ቁመው ይታያሉ በቅዱስነታቸው አስከሬን ዙሪያ ሆነው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት መዝሙረ ዳዊት ይጸልያሉ ከአስከሬኑ ራቅ ብለው በስተቀኝ ሁለት በስተግራ ሁለት የክብር ዘቦች ቀጥ ብለው ቁመዋል ። ከሌሊቱ ፬ ሰዓት ጀምረው ስብሐተ ማኅሌት ሲያደርሱ ያደሩ መዘምራን ክሥተት አርያም አድርሰው እስመ ኪያከ ዘመው ያመረግዱ መረግዱ አልቆ ከተፀፋ በኋላ ቅኔው ተጥሏል በዚያን ጊዜ የተደረሱትም ቅኔዎች በሌላ ጽሑፍ ተመዝግበዋል ።

ከጧቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ውዳሴ ማርያም ተደገመና ጸሎተ ፍትሐት በእንተ እለ ኖሙ ይደርስ ጀመር በጸሎቱም ላይ

ብፁዕ ዘኀረይኮ ወዘተወከፍኮ ወዘአኀደርኮ ውስተ አዕፃዳኪ ጸገብነ እግዚአ እምበረከተ ቤትከ የሚለው መዝሙረ ዳዊት ተሰብኮ ከሉቃስ ወንጌል ምዕ ፲፱. ፲፪ ጀ፳ ተነበበና ጸሎተ ፍትሐቱ እስከ ፫ ሰዓት ቀጥሏል ።

<u>፫ ሰዓት ሲሆን</u> በሰበታ ደናግል ጠባባት ገዳም የሚኖሩ መነኮሳይያት ጥቋቁር ቀሚስ ለብሰው ጥቋቁር ካባ ደርበው ጥቋቁር ቆብ ደፍተው ጥቋቁር ሼማ በማድረግ ወደ ቅዱስነታቸው አስከሬን ቀርበው ኃዘናቸውን ሲገልጹ በዚያ የነበረውን ኀዘንተኛ ሁሉ አልቅሰው አስለቀሰውታል ።

ከእነርሱም በመቀጠል በዚሁ ገዳም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሚረዱ ዕጓለ ማውታ ሕፃናት ወደ ቅዱስነታቸው አስከሬን በመቅረብ ኀዘናቸውን ገልጸዋል ።

<u>፬ ሰዓት ከሩብ ሲሆን</u> በካቴድራሉ ውስጥ ያለው ኀዘንተኛ ሁሉ ወደ ውጭ በመውጣት በየተመደቤተ ክርስቲያን እየተረዱ የሚያድጉ ሕፃናት የተለየ አንድ ዓይነት ቀሀና ልብስ ለብሰው በካቴድራሉ ዙሪያ ተሰለፉና ቆሙ ።

<u>፭ ሰዓት ሲሆን</u> ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ባለመጾር መስቀል የያዙ ፮ ዲያቆናት በቅዱስነታቸው አስከሬን በስተኋላ በሰልፍ ቆሙ ከአንርሱ ቀጥለው የቅዱስነታቸውን የክብር ዕቃዎች የያዙ ፬ መነኮሳት ተሰለፉ ቀጥሎም ጥቋቁር ልብስ ለብሰው ጥቋቁር ቆብ የደፉ መነኮሳት የቅዱስነታቸውን አስከሬን



በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አበባ ሲያስቀምጡ

በለት ቦታ በሰልፍ እንዲቆም በሊቀ ሥልጣናት ሀ ማርያም ወርቅነህ የትንግኤ አሳታሚ ድርጅት ሐላፊ አማካይነት ተነገረው ።

በመርሐ ግብሩ መሠረት ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን ዩኒፎርም የለበሱ የሰንበት ተማሮች የቅዱስ ጳውሎስ ከመ ት ተማሮች የመለዮ ልብሳቸውን ለብሰው ከስበታ ደናግል ጠባባት ገዳም የመጡ መነኮሳይያት ጥቋቁር ልብስ ለብሰው በዚያው ገዳም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተሸክመው አስከሬኑ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ግራና ቀኝ ታጅቦ ወደ ዓውደ ምሕረቱ በወጣ ጊዜ ሁሉም እንባ በእንባ ይራጭ ጀመር የቤተ ክርስቲያኑም ደወል ለአምስት ደቂቃ ጩኸቱን አሰተጋባ ።

አንድ ጊዜ ሁደት እስከሚደረግ ድረስ ሰልፈኞቹ ከቆሙበት ቦታ ሳይንቀሳቀሱ የኀዘን መዝሙር ይዘምሩ ነበር የወላይታ ብሔረሰብ አባላት ግን የባህል መግሪያቸውን እየነፉ በአስከሬኑ ፊት ለፊት በመኳዝ ያለቅሱ ነበር



www.ethiopianorthodox.org

ጥንግ ድርብ ካልበሱ መዘምራንም በከፊል አስከሬትን እየተከተሉ "ሰማዕኩ ጸሎተከ ወሰዕለተከ እምብዙኅ ፃማ አእርፈከ ኀበ ሀሎ ፍሥሐ እነብረከ" የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር ይዘምሩ ነበር ።

አንድ ጊዜ ዑደት ከተደረገ በኋላ የቅዱስነታቸው አስከሬን ተመልሶ ከነባረበት ቦታ አርፏል ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ የግሪክ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በቅዱስነታቸው አስከሬን አጠገብ ቆመው ጸሎተ ፍትሐት ከማድረሳቸውም ሌላ ጽንሐሕ ይዘው በዚያው ውስጥ ፍሕምና ዕጣን በማድረግ የቅዱስነታቸውን አስከሬን እየተዘዋወሩ በአራቱ ማዕዘን በማጠን የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸዋል ። እንዲሁም ቅዱስነታቸውን በቅርብ ከሚያውቋቸው የወላይታ ብሔረሰብ አባላት በቅዱስነታቸው አስከሬን አጠገብ የባሕል መሣሪያቸውን እየነፉ መሪር የሆነ ኀዘናቸውን ገልጸዋል።

<u>፮ ሰዓት ከ፲፭ ደቂቃ ሲሆን</u> ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሯል የተቀደሰውም በሥስቱም መናብርት ነበር ጸሎተ ቅዳሴው የተመራው በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሲሆን የመሩትም

፩. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
፪. ,, ,, መርሐ ክርስቶስ
፫. ,, ,, አቡነ ቶማስ
፬. ,, ,, ኤልሳዕ
፭. ,, ,, ኤልያስ
፮. ,, ,, ያዕቆብ ናቸው ።

በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ከመዝሙረ ዳዊት የተሰበከው "ብፁዓን ኩሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ቤትከ ወለዓለመ ዓለም ይሴብሑከ ብፁዕ ብእሲ ዘእምኅቤከ ረድኤቱ እግዚእ" የሚለው ነው ከወንጌልም የተነበበው የሐንስ ምዕ ፲፬ ፩—፯ ሲሆን ያነበቡት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ናቸው "ጸሎተ ቅዳሴው በ፰ ሰዓት እንደተፈጸመ በዑደት ጊዜ እንደተደረገው ዝግጅት ተጀመረ።

ልብሰ ተክህና ለብሰው ባለመጾር መስቀል የያዙ ስድስት ዲያቆናት በቅዱስነታቸው አስከሬን ፊት ለፊት በሰልፍ ቆሙ ። የቅዱስነታቸውን የክብር ዕቃ የያዙ አራት መነኮሳት ከዲያቆናቱ ቀጥለው በስተኋላ ቆሙ ።

ጠብመንጃ የያዙና የሙዚቃ መሣሪያ ያነገቡ የክብር ዘቦች መጥተው ከካቴድራሉ መውጫ በር እንሥተው እስከ ቅዱስነታቸው መካነ መቃብር ድረስ በዓውደ ምሕረቱ ግራና ቀኝ ተሰልፉ ወዲያው ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የኮር ዲፕሎማቲክ አባላት የተመደበላቸውን የክብርቦታ እንደያዙ ጥቁር ልብስ በለበሱ መነኮሳት ግራና ቀኝ ተደገፍ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታጅቦ የቅዱስነታቸው አስከሬን ወደ ዓውደ ምሕረቱ ብቅ ሲል በዚያ ተሰልፎ የነበረው የክብር ዘብ በብረት ሰላምታ አቀረበ የክብር ዘብ ሙዚቀኞችም የኀዘን ማርሽ አሰሙ የአብያተ ክርስቲያናት ደወሎችም ለ፳ ደቂቃ አስተጋቡ ፎቶ ግራፍ አንሽዎችም ፎቶ ለማንሣት መሣሪያቸውን እንደሰማይ ቁጣ ብልጭ ድርግም በማድረግ ያብለጨልጩ ጀመር ቪዲዮና ቴሌቪዥን አንሽዎችም ሥነ ሥርዓቱንና ድርጊቱን ቀርጾ ለማስቀረት ይረባረቡ ጀመር ።

ከዚህ በኋላ አስከሬኑ በዓውደ ምሕረቱ ላይ አርፎ በአንተ እለ ኖሙ ሲጸለይ ከመዝሙረ ዳዊት ። ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር ፡

እግዚኦ አነ ገብርከ ።

ገብርከ ወልደ ዓመትከ የሚለው ተሰብኮ የማቴ. ወንጌል ፳፭ ፩—፲፮ ተነቦ ሲያበቃ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የመንበረ ፓትርያርክ ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳስ የቅዱስነታቸውን የሕይወት ታሪክ ባጭሩ አነበቡ ከዚያም አስከሬኑ ወደ መካነ መቃብሩ ተወስዶ አፈር ከመመለሱ በፊት ሊቃነ ጳጳሳት መስቀል ይዘው አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው ከጸለዩ በኋላ ሥርዓተ ቀብሩ ተፈጸሚል በዚያም ጊዜ የክብር ዘቡ በብረት ሰላምታ ሲያቀርቡ ሙዚቀኞችም የኀዘን ማርሽ አሰምተዋል ። የአብያተ ክርስቲያናት ደወሎችም ለጥቂት ደቂቃ ድማፃቸውን አሰምተዋል ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የመንበረ ፓትርያርክ ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳስ በቅዱስ ሲኖዶስ ስም ፡

ጓድ ተፈራ ወንዴ ም ጠ/ሚኒስቴር በመንግሥት ስም

ሊቀ ማእመራን ደምፀ ገብረ መድኅን በጠ/ቤተ ክህነት ስም አበባ አስቀምጠዋል ሌሎችም አበቦች በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል ከዚያም በኋላ ብፁዕነታቸው

፩ኛ/ የቅዱስ ፓትርያርኩን ሕይወትለማትረፍ

፪ኛ/ ከሞቱ ጀምሮ እስከሚቀበሩ ድረስ የችግሩና የኀዘኑ ተካፋይ በመሆን ዓብዮታዊው መንግሥት ስላደረገው ትብብር በቤተ ክርስቲያን ስም አመስግነው ጸሎተ ቡራኬ አድርገዋል ።

ከዚያም በኋላ ክቡራን ሚኒስትሮች ለኀዘኑ ተካፋይ በመሆን የመጡ እንግዶች ሁሉ ከብፁዕ አቡነ አብርሃም የመንበረ ፓትርያርክ ተጠባባቂ ሊቀ ጳጳስ እየተሰናበቱ ወደየመጡበት ሲመለሱ የኮር ዲፕሎማቲኮች አባላትና ሌሎችም ። በተዘጋጀው የክብር መዝገብ ላይ የተሰማቸውን ኀዘን እየገለጹና እየፈረሙ ብፁዕነታቸውንም እጅ እየነሡ በመሰናበት ወደ የቤታቸው ተመልሰዋል ።

ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ሲሆን በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የቅዱስነታቸው የቀብር ሥነ ሥርዓት ተፈጸሞ ኃዘንተኛው በሙሉ ወደ መንበረ ፓትርያርክ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተመልሷል ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሞት ቤተ ክርስቲያናችን መሪር የሆነ ኃዘን ተሰምቷታል ። ቢሆንም መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ የሚለውን ቃል ስለምታምን ኃዘኗ እንደ አሕዛብ የቀቢጸ ተስፋ ኀዘን አይደለም ።

ዓበይተ ነቢያት ሲያልፉ ደቂቀ ነቢያትን ፡ ሐዋርያት ሰብአ ፡ አርድዕት ሲያልፉ ሊቃውንትን መምህራንን በየጊዜው እያሥነሣ ሕዝቡን ሲመክር ሲያስተምር የኖረ አሁንም ያለ ወደፊትም ለዘለዓለም የሚኖር አምላክ እንደቅዱስነታቸው ያለ ቸርና ርኅሩኅ በሚሠራው ሥራ ሁሉ መልካም አርአያነት ያለው ታላቅ አባት እንዲተካላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንችን ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለች ።

ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ

በባብጎ

---

# የደስታ ዋስትና ምን ይሆን?

(ከገጽ ፳፱ የዞረ)

ሀብት ቢሰበሰብ የደስታ ዋስትና አይሆንም ምክንያቱም ወይም ቀድሞህ ይሄዳል ወይም ወደኋላህ ይቀራል እንጂ አብሮህ ለመኖር የታመነ አይደለም ሰላም ግን እስከ መቃብር አብሮ የሚኖር የማይከድ ጥብቅ ጓደኛ ነው የሰላም አስፈላጊነት ስንኳን ለራሰም ለሌላም ሰው መጸለይ እንደሚገባ አስታውሶ ነቢዩ ኤርምያስ የጠቀሰውን ብናስታውስ መልካም ነው (ሕዝ ሰላማ ለብሔር) በእሷ ሰላም የእናንተ ሰላም ይደረጋልና እናንተን አስማርኬ ባሳደድኋችሁ አገር ለሀገራቱ ሰላምነታዋን ፈልጉ ወደ እግዚአብሔርም ስለሷጸልዩብሏልኤር·፳፱፣፯ ፫።

እንግዲህ ሰላምን መፈለግ ራስን ማዳን ነው ራስንም መጠበቅ ነውና ሰላምን እንያዝ ።

መ/ክነፈ ርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

# ታማኝ አገልጋይ

ታማኝና ትጉህ ሠራተኞች በማናቸውም የሥራ መስክ አስፈላጊ በመሆናቸው እንደችሎታቸውና በተፈለጉበት ቦታ ቃል ገብተው ይቀጠራሉ ። ከተቀጠሩም በኋላ በእውነት ሠርተው በሚያሳዩት ውጤት የሚሾሙና የሚሸለሙ ብዙዎች እንደመሆናቸው ፡ በልግመኛነትና በእምነት አጉዳይነት የሚጠበቅባቸውን መልካም ውጤት ማስገኘታቸው ቀርቶ በሚያስከትሉት ጉድለትና ጥፋት እራሳቸውን ለፍርድ አጋልጠው በችግር ላይ የሚገኙ ጥቂቶች አይደሉም ።

ለደግም ሆነ ለክፉ ሥራ በፍርድ ቀን ለሁሉም እንደሥራው ዋጋውን ለመክፈል ጥያቄ እንዳለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ በሚያስተምርበት ጊዜ እንዲህ ሲል ያስረዳል ።

አንድ ወደእሩቅ አገር የሚሄድ ሰው ሦስት ሠራተኞቹን ጠርቶ ለአንዱ አምስት ፡ ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ መክሊት ሰጥቶ እየነገዱበት እንዲቆዩ አደረገ ። በተመለሰም ጊዜ ገንዘቡን ለመቆጣጠር አስጠራቸው ። አምስት የወሰደው ሌላ አምስት አትርፎ መለሰ ጌታውም "አንተ ታማኝ አገልጋይ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ ሂድ ወደጌታህ ደስታ ግባ" አለው ። ፪ኛውም ሌላ ሁለት መክሊት አትርፎ መለሰ ። ጌታውም "አንተ ታማኝ አገልጋይ በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ ፡ ወደጌታህ ደስታ ግባ" አለው ። ፫ኛውም ቀርቦ አንድ መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር ። ያልዘራኸውን የምታጭድ ያልበተንኸውን የምትሰበስብ ጨካኝ መሆንክን አውቄ ስለፈራሁ በመሬት ቀብርሁት መክሊትህ ይኸው አሉ ፡ ጌታውም አንተ ሰነፍ አገልጋይ ይህን ሳደርግ ታውቃለህ? ካወቅህስ ለምን ገንዘቡን ተቀብለህ ወጥቶ ወርዶ ለሚያተርፍ አሰጠው አልነበረም ። ላለው ይሰጠዋል ለሌለው ግን ያው ይወሰድበታል በማለት ያኑ አንዱን መክሊት ለባለአሥሩ እንዲሰጡትና እሱ ወደዘላለም ጨለማ እንዲገባ አዘዘ ። ማቴ ፳፭ ፡ ቁ ፲፬—፴ (አንድ መክሊት ፺፪፻ሺህ ግራም ያህል ነው ።)

ከዚህ ትምህርት የምንረዳው በአጠቃላይ የሥራን ክቡርነትና ሰው በተሰጠው ጉልበት ፡ ሀብትና ዕውቀት ሠርቶ እንዲጠቀም ፡ እንደትጉሆቹ ሠራተኞች ወጥቶ ወርዶ ባገኘው ሀብትና ንብረት ተደስቶ እንዲኖር ኋላም በፍርድ ቀን የማያልፈውን ሹመትና ሽልማት እንዲያገኝ ነው ።

ለእያንዳንዳቸው ሠራተኞች እንደችሎታቸው ገንዘብ ሰጥቶ እየነገዱበት እንዲቆዩ ያደረገው ሰው ምሳሌ እራሱ ክርስቶስ ነው። ለሁሉም እኩል አለመስጠቱ ሰው በተፈጥሮው እኩል ቢሆንም ችሎታውና ፡ አቋሙ አንድ አለመሆኑንና የእግዚአብሔርም ስጦታ የተለያየ መሆኑን ያስረዳል ላንዱ ብዙ ላንዱ ጥቂት መስጠቱም ሰው በተሰጠው ነፃ አእምሮ በማሰብ ባለው ዕውቀትና ጉልበት ተግቶ ከሠራ ትንሹ ትልቅ ፡ ድሀው ሀብታም እንደሚሆን ለማሳብ እንጂ "እግዚአብሔርስ ለሰው ፊት አያዳላም" ተብሏል ።

ሥራን የሚያሳድገው እራሱ ሠራተኛው ነው ። ሁሉም በየተሰማራበት በርትቶ ከሠራ በሥራው ልክ ዋጋው ስለሚከፈለው በሰው ዘንድ ድህነት የሚባል ነገር አይኖርም ። ለእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው "የሚለውም የኅብረተሰብአዊነት ፍልስፍና ይኸው ነው ።

ነጋዴው ወጥቶ ወርዶ በሐቅ ነግዶ ካተረፈ ፡ ገበሬው በወቅቱ ዘርቶና ሰብስቦ ካመረተ እድሚልኩን ተደስቶ ይኖራል ። በተለያዩ መ/ቤቶችና ፋብሪካዎችም እንደችሎታቸው የተሰማሩ ባለሙያዎች በትጋትና በታማኝነት ከሠሩ እራሳቸውን አክብረው ለሀገራቸው እድገት ፡ ለወገናቸው ኩራት ናቸው ለሌሎችም መልካም አርአያ ይሆናሉ ፡ ይሾማሉ ፡ ይሸለማሉ የደሞዝ ጭማሪ ይደረግላቸዋል ። ከዚህም የበለጠ ደስታ የለም ።

እንደባለአንዱ መክሊት ያሉ ልግመኞችና ሰነፎች ግን ታማኝነትም ስለሚጐድላቸው ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን ቀብረው ፡ ለሀገር ሸክም ለወገን አሳፋሪ ናቸው ።

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ከልማታቸው ጥፋታቸው ስለሚያመዝን በመሾምና በመሸለም ፋንታ የያዙትን ይነጠቃሉ ፡ ይቀጣሉ ፡ ከሥራም ይባረራሉ ። እስከመጨረሻው ድረስ አወዳደቃቸው የከፋ ይሆናል በዚህም ጊዜ እነሱ እንደሚያስቡት ትጉህ ሠራተኞች የሚያድጉት በሥራቸው ሳይሆን በወገን ፡ በአድልዎና በተለያየ መንገድ እንደሆነ አድርገው ነው ።

ሰነፎች ምንጊዜም ቢሆን የራሳቸውን ሥራ ጠልነት አያስቡም ከስንፈታቸውና ከእምነት አጉዳይነታቸው የተነሣ የሚደርስባቸውን ውድቀት ሌላ ሰው እንዳመጣባቸው ቆጥረው የሌላውን ስም ማጥፋትና ማማት ልማዳቸው ነው ።

ሳይሠሩ "የእድሌን አላጣውም፡ እሱ የከፈተውን ጉረሮ ሳይዘጋው አያድርም" እያሉ መና ከሰማይ እስከሚወርድላቸው የሚጠብቁ ለሰውም ለእግዚአብሔርም ያልተመቹ ናቸው ። ያለሥራ የበለፀጉ እስካሁን ድረስ በዓለም ላይ አልታዩም ። ሳይሠሩ ራበኝ ፡ ጠማኝ ፡ በረደኝ ፡ ብሎ እግዚአብሔርን ማማረር "በፊትህ ወዝ ትበላለህ" የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ አፍርሶ በራስ ላይ መፍረድ ነው ።

በየትኛውም ቦታ ሰነፎች ስለማይጠፉ በቤተ ክርስቲያናችንም ወርቁን በመቅበር ያለትርፍ አምክኖ እንዳስቀረው ገብር ሐካይ (ክፉ አገልጋይ) ያሉ አገልጋዮች እየበዙ ሲሄዱ እናያለን ። ዕውቀታቸውን በጋን ውስጥ እንዳለ መብራት አፍነው ይዘው የማያስተምሩ፡ የተሰጣቸውን ሥልጣን በማይስማማው ቆሻሻ ነገር የሚያበላሹ ጥቂት አይደሉም ። የራሳቸው ጥቅም ብቻ እንዲጠበቅላቸው እንጂ መንጋውን አውሬ ቢነጥቀው ደንታ የሌላቸውን ምንደኞች ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ ትፋረዳቸዋለች ። "ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚወጠብቁ እረኞች እንዲህ ይላል በጎችን በትናቸኋል፡ አባርራችኋቸውማል ፡ አልጎበኛችሁም እነሆ የሥራችሁን ክፋት እጐበኛለሁ" ይላል ኤር ፳፫ ፡ ፪ ።

ከሁሉም ይልቅ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው አገልግሎት መንፈሳዊ እንደመሆኑ መጠን እውነተኞች አገልጋዮች ያስፈልጋሉ ያልተማሩትን የሚያስተምሩ፣ያላመኑትን የሚያሳምኑ ፡ ያመኑትንም የሚያጸኑ ፡ ያዘኑትንም የሚያረጋጉና ምእመናንን የሚያበዙ ካህናት የጥብርኄር (የታማኙ አገልጋይ) ምሳሌዎች ናቸው ። እነዚህ በተሰጣቸው ሥልጣን ፣ በቀሰሙት ትምህርት ወጥተው ወርደው አስተምረውና አሳምነው ብዙ ክርስቲያኖችን አትርፈዋልና ። እናንተ በጥቂቱ የታመናችሁ በብዙ እሾማችኋለሁ" ባለው መሠረት ሹመትን ሽልማታቸውን ያገኛሉ ። ትድላና ደስታ የተመላበት የዘለዓለማዊ መንግሥት ባለቤት ይሆናሉ ።

ሰው በተሰጠው ዕውቀትና ጉልበት ካልሠራበት ሌላ ማግኘት ቀርቶ ያው ያለው ሀብት እንኳን እንደማይባረክለት ሲያስረዳ "ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ለሌለው ግን ያው ይወሰድበታል" ሲል በቁ ፳፱ ላይ ያብራራል ። ሀብታሙ ለሠራተኞቹ ወጥተው ወርደው ፡ ነግደው አትርፈው እንዲቆዩት ገንዘቡን ሰጥቷቸው የሄደው ቀናውንም ሆነ ከትርፉ ለራሱ ጥቅም ፈልጐ አይደለም ። ማንም ሰው በሕይወተ ሥጋ ሳለ ሠርቶ ባገኘው ሀብት ተደስቶ ፈጣሪውን እያመሰገነ እንዲኖር ሀብተ ሥጋን አትርፎ እንዲኖር ፡ ሀብተ ነፍስንም አትርፎ ዘለዓለማዊት የሕይወት ኑሮን እንዲኖር ነው ።

ትምህርቱንና ምሳሌውን ወደ ራሳችን መለስ አድርገን ማሰብ ሲገባን እንዲሁ አንብበን የምንረሳው መሆን የለበትም ። እኔስ የቱን እመስላለሁ ? ባለአንዱን ወይስ ባለ ሁለቱንና ባለ አምስቱን መክሊት ብለን መመርመር አለብን ሥራችን የባለአንዱን መክሊት መስሎ ከተገኘ ቀን ሳይወስን ለመልካም ሥራ ታጥቀን መነሣት እንዳለብን ነው ለማናቸውም ሥራ ቆራጥና ታማኝ መሆን ያስፈልጋል ፤ ፍርሃት ፣ ጥርጣሬና ማወላወል በልቡናችን ከገባ ግን ሥራችን ሁሉ ፍሬ ቢስ ሆኖ እንደሚቀር ከዚህ ትምህርት መረዳት አስፈላጊ ነው ።

"መድኃኒታችን ክርስቶስ የምንሠራባቸውን ጤናማ አካላት ፡ ከእውቀት ጋር ሰጥቶ በዚህ ዓለም የሥራ መስክ ላይ አሠማርቶናል ታዲያ ሊቆጣጠረን በመጣ ጊዜ በሰጠሁህ ሀብት ምን ሠራህ ? የቱን አተረፍህ? ብሎ ሲጠይቀን መልሳችን የባለአንዱን ሳይሆን የባለሁለቱንና የባለአምስቱን መክሊት መሆን ይገባዋል ። ይህ ከሆነ "በብዙው እሾምሃለሁ" የሚለው ቃል ለኛ መሆኑን ያረጋግጥልናል ።

መ/መንክር ዋሴ

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ኤጲፋንዮስ የተባለውም ሊቅ.. ወረፈቀ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ቤተ አልዓዛር አርኩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወዳጁ በአልዓዛር ቤት ተቀመጠ ይላል

በወዳጁ በአልዓዛር ቤት በማዕድ ተቀምጦ ለደቀ መዛሙርቱ ስለሐዲስ ኪዳን የሚሠዋው ሥጋውን በኅብስት የሚፈሰውን ደሙን በወይን መስሎ ገልጾላቸዋል ብዙዎች መጻሕፍትም ማዕዱ የተዘጋጀው በአልዓዛር ቤት እንደሆነ ይናገራሉ በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን የጸሎተ ሐሙስን ምሥጢር የፈጸመው ከሦስቱ አደራሾች በየት.

(ወደ ገጽ ፲፱ የዞረ)





www.ethiopianorthodox.org

# አንድነትና ሦስትነት

## በአብርሃም ቤት

ሥላሴ ተብለው የሚጠሩት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። በአካል ሦስት ብለን በመለኮት ግን አንድ አምላክ ብለን እናምናለን ። አንድነታቸውንም የሚገልጽ በቅድምና በመኖር በፈቃድ ፤ በመፍጠር በመስጠትና በመንሳት በመግደል በማዳን በፍጹም አምላክነት ነው ።

በመፍጠር አንድ ሲሆኑ እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር ዘፍጥ /፩፥፳፮/ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ቀድም አድርጐ በፈጠራቸው በመላዕክት መልክ ሳይሆን በራሱ መልክና ቅርጽ ፈጠረው (ዘፍ· ፩፥፳፯)

እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነውና በሐዲስ ኪዳንም በማቴዎስ ወንጌል እነሆ ሰማዮች ተከፈቱለት የእግዚአብሔር መንፈስ እንደርግብ ሲወርድ አየ በራሱም ላይ ሲቀመጥ ከሰማይም ድምፅ መጣና የምወደው ልጄ ይህ ነው ሲል እግዚአብሔር አብ መስክሯል ። እግዚአብሔር ወልድም በዮርዳኖስ ሙኳኵሖ ቆሞ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ የገለጸው ምስክር ለእግዚአብሔር ሦስት አካል እንዳለው ያስረዳል ።

ሥላሴ ማለት ሦስትነትን የሚያስገነዝብ ነው ለአንድነቱም ሁለተኛነት ለሦስትነቱም አራተኛነት የለውም እንግዲህ የምሥጢረ ሥላሴ ምሏትና ስፋት በመጠኑ ይህን ይመስላል ።

ወደ አሁኑ የሥላሴዎች ሞቃሰ ቢያ በዓል ስናስታውስ ሐምሌ ፯ ቀን የሚከበረው ዓመታዊ የሥላሴ በዓል የእግዚአብሔር ባለሟልና ፍጹም ታማኝ የነበረው አብርሃም ሥላሴን በእንግድነት የተቀበለበትና ተስፋውን የሰማበት ዕለት እንደሆነ ይነገራል ።

እንግዲህ ከአብርሃም የምንወስደው ታላቅ ትምህርት አለ የሰው ልጅ ሁሉ በጐ አድራጐት ከጀመረ በኋላ መመለስ እንደማይገባ ነው ። የአብርሃም የዕለት ተግባሩ እንግዶችን መቀበል ሲሆን ይህንን የተቀደሰ በጐ አድራጐት እንዲያቋርጥ በሰይጣን አማካይነት ብዙ ፈተና ደርሶበት ነበር ። ይሁን እንጂ ከዚህ የጽድቅ ተግባር ሊገታ አልቻለም ። ክብሩም እየበዛለት ሄደ እንጂ አላነሰም ። ቀድም ሲል እንግዶች ይቀበል የነበረ ሰዎችን ነበር ኋላ ግን ሥላሴን በእንግድነት ለመቀበል በቅቷል ።

በቀትር ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ተቀምጦ በውጭ ሲመለከት ሳለ ሥላሴዎች ተገልጠው ስለታዩት ሊቀበላቸው ሮጦ ሄዶ ሰገደላቸውና ለግብዣ ወደ ድንኳኑ እንዲገቡ ጠየቃቸው ወዲያውም ገብተው በግብዣው ላይ ተነስተው ባርከውታል ። በዚህም አጋጣሚ ጊዜ አንድነታቸውንና ሦስትነታቸውን ሊአውቅ ችሏል ። (ዘፍ· ፲፰·ቁ፩–፲፰) አብርሃም ይህንን ታላቅ ክብር ለማግኘት የበቃው በሃይማኖትና በሥነ ምግባር በመጽናቱ ነው ። በዚህም የእግዚአብሔር ማደሪያ ሆኗል ። እርሱም ሕጉን የጠበቀ ቢኖር ወደ እርሱ እንመጣለን በርሱም ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን ብሏል (ዮሐ፲፬·፳፫) አብርሃም የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን በእግዚአብሔር ስለተመረጠ የመጨረሻው የተስፋ የምሥራች ከእግዚአብሔር ተነግሮታል ።

የተስፋውም ቃል እንዲህ የሚል ነበር የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እንመለሳለን (ዘፍ፲፰፥፲) ለጊዜው የተነገረው ተስፋ ሚስትህ ሣራ ልጅ ትወልዳለች የሚል ነበር ። ነገሩ ቢደንቃት በእድሜ ያረጀች መሆንዋና ባለቤቷ አብርሃምም የሸመገለ መሆኑን ገምታ ከእንግዲህ ልጅ ልወልድ ይቻላልን ብላ በመጠራጠር ስቃ ነበርና ሣራ ለምን ሳቀች ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን የሚል ቃል ከእግዚአብሔር ከተነገራት በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል ማንም ሊያስተባብለው ስለማይችል ፀነሰችና ወለደች ስሙንም ይስሐቅ አለችው ።

አብርሃም የኖረው ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ነው ። ከሞት በኋላ ለስሙ መታሰቢያ የሚሆን ግዙፍ ሐውልት አልተሰራለትም። ነገር ግን አብርሃም በዘመናት ሁሉ የሚዘከርበት አንድ መታሰቢያ አለው ። ''አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ'' እንዲል

አብርሃም ታላቅ የሃይማኖት አባት የምእመናን ሁሉ አርአያ ያደረገው በእግዚአብሔር መታመኑ ነው ። ይህም እምነቱ በሰው ፊት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ዋጋ አስገኝቶለታል ።

አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ከዚህ የበለጠ ነዋሪ መታሰቢያ ሊኖር አይችልም ። እገሌ በእግዚአብሔር ይታመናል የሚለው ምስክርነት ከማንኛውም ገናና ክብር የበለጠ ነዋሪነት ያለው መታሰቢያ ነው ።

ክርስቶስን በእምነት የሚቀበል ሰው የዘላለምን ደኅንነት ያገኛል ስሙም በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይጻፋል ።

ስለዚህ ነው በእግዚአብሔር መታመን የእግዚአብሔርን ተስፋ በእምነት እጅ መጨበጥ ቀዋሚ የሆነ መንፈሳዊ ጥቅም ሊያስገኝ የሚያስችለው ። ሌላው ሁሉ ሃላፊና ጠፊ ነው ። እንግዲህ እኛም እንደአብርሃም በእምነት ሥላሴዎችን ለማስተናገድ ልባችን ይዘጋጅ ።

መምህር ተወልደ መድኅን
ገ/ሥላሴ

# ዜና ሊቃውንት

## የብፁዕ አቡነ አብርሃም አጭር የሕይወት ታሪክ

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሐምሌ ፳ ቀን ፲፰፻፺፩ ዓ/ም በጐጃም ሀ ስብከት ሞጣ አውራጃ አሸመን ከተባለ ቦታ ተወልደው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት አንድ መምህር እየተማሩ አደጉ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ዘእምንዕሱ ሕይወቱ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ከሕፃንነቱ ጀምሮ ዕድገቱ በቤተ እግዚአብሔር ነው ተብሎ እንደተነገረው ከሕፃንነታቸው ጀምረው በመንፈሳዊነትና በትሩፋት ሥራ ኑሯቸውን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ስላደረጉ ሕሊናቸው ሁሉ በፍቅረ እግዚአብሔር ጽሙድ ሆነ ከዚህም የተነሣ ወደ መንፈሳዊ ትምህርት እያደሉ በየትምህርት ቤቶች እየዞሩ በመጀመሪያ ፀዋትወ ዜማን ቀጥሎም ቅኔን ከእነአግባቡና ከእነ ምሥጢሩ አወቁ ።

አቡነ አብርሃም አንድ ጊዜ የትምህርት ፍቅር አድሮባቸዋልና ወደ መምህራን መጻሕፍት እየሄዱ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምረውና ተመራምረው ተረድተዋል፡ ይልቁንም ቦሩ ሥላሴ ከነበሩት መምህር አካለ ወልድ ዘንድ ሄደው ከሌሎች መምህራን የተማሩትን ትምህርት ሁሉ አጥርተው በመማራቸው ሊቅነታቸው ከፍ ያለ ሆነ ።

አራቱን ጉባኤዎች ደኅና አድርገው ስላወቁ ገና በተማሪ ቤት ሳሉ ተማሪው ሁሉ ለመምህርነት አጫቸው ስለዚህ እርሳቸው በአንድ ወገን ከመምህር አካለ ወልድ ሲማሩ በአንድ ወገን ደግሞ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ነበር ፡ ለጠየቃቸው ሁሉ የሚገባውን መልስ ሲሰጡ ሰሚውን ሁሉ ያስደንቁ ነበር ።

ቦሩ ከመምህር አካለ ወልድ እየተማሩ በማስተማር ብዙ ቀን ከተቀመጡና ትምህርቱን ሁሉ ከጨረሱ በኋላ ለማስተማር ወደ ሌላ ሀገር በሄዱ ጊዜ ተማሪው ከየአለበት እየወጣ እንደ ንብ ከበባቸው እርሳቸውም እንደማር የጣፈጠ ቃልን ያስተምሩት ጀመር ይህም ዝናቸው በመላው ኢትዮጵያ ስለተሰማ ሁሉ ከጉባኤያቸው ተቀምጦ የእርሳቸው ደቀ መዝሙር ለመሆን ፈለገ እግዚአብሔርም እንደአባታቸው አብርሃም ለብዙ ሕዝብ መንፈሳዊ አባት ሊያደርጋቸው ፈቃዱ ስለሆነ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ አደረገ አዲስ አበባም እንደ መጡ ሳይውሉ ሳያድሩ የአዲስ አበባ ቅዱስ ገብርኤልን እልቅና ተሾሙ ከተሾሙም በኋላ ጉባኤያቸው ከቀድሞው ይልቅ እየሰፋ ሄደ አዲስ ለሚማረው ሐዲስ ፡ ሊቅ ለሚማረው ሊቅ ብሉይ ለሚማረው ብሉይ እንዲሁም አስተምሩኝ እንዳላቸው ያስተምሩ ጀምር ሲያስተምሩ ተማሪው እንዳይቸገር እየበሉ እያጠጡ እያለበሱ ነበር ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በዚህ ትምህርታቸውና በመንፈሳዊነታቸው ተመርጠው ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አቡነ አብርሃም ተብለው ተሾሙ የመጀመሪያው ስማቸው መምህር ደስታ ነበር ።

ከሀገራችንም ያን ጊዜ ከተሾሙት ጳጳሳት በመዓርግ አንደኛው እርሳቸው ነበሩ የጵጵስናውን ሹመት ከተቀበሉ በኋላ ጐጃምና ጐንደር ሀገረ ስብከት እንዲሆኗቸው ስለተመደቡ ከዚያ ወዲህ አንድ ጊዜ ጐጃም አንድ ጊዜ ጐንደር እየተመላለሱ ቃለ እግዚአብሔርን እንደዘር እየዘሩ በምእመናን ልብ አብቅለዋል ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ትሕርምትን ያበዙ ነበር ፡ ልባቸው በመጻሕፍት ፍቅር ያነደደ ስለሆነና መጽሐፍትን መመልከት ስለሚያበዙ ዓይናቸውን ታመው ሲቸገሩ ሳሉ በሕክምና በመረዳት ሊድኑ ችለዋል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ትሕር





www.ethiopianorthodox.org

ምት ስለሚያበዙ እንጀታቸው እየደረቀ ታማሚ ሆነው ነበር ምንም ቢያማቸው በጭንቅ ተዳ ዘው ከአልጋ ላይ እስከሚውሉ ድረስ ለሕዝበ ክርስቲያኑ መል ካም ምክራቸውን ከመስጠት አላ ቋረጡም ነበር ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ዕንግዳ ተቀባይ ለደሃ እናት ለቸገረው ረዳት እጅግ መልካም አባት ስለነ በሩ ሕዝቡ እውነተኛው አብር ሃም ይሏቸው ነበር ።

አንድ ጊዜ ደግነታቸውና ዕን ግዳ ተቀባይነታቸው በሁሉ ሰው ዘንድ ታውቋልና የተቸገረው ከሩቅ ሀገር የመጣው ሁሉ ማረፊ ያው ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ግቢ ነበር ፡ እርሳቸውም ለሁሉም ድርጎ እየሰጡ በመልካም ሁኔታ ያስተምሩት ነበር ።

በኋላም በጠና ታመው ሲታ ከሙ ቆይተው ነበር ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወሰነውን ዘመን ለማለፍ አይቻልምና ሐምሌ ፳፬ ሰኞ ከጠዋቱ ልክ አንድ ሰዓት ተኩል ፲፱፻፴፩ ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ በሞታቸ ውም የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲ ያን ኀዘን ተሰማው የጻድቅ ሞቱ በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው። እንደተባለው ሕዝበ ክርስቲያኑ በዚህ ቃል ሊጽናና ችሏል ።

ዕረፍታቸውም በየአድባራቱና በየገዳማቱ በተሰማ ጊዜ ሁሉም አዝኗል ቀብራቸው የሚፈጸመው ሐምሌ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፩ መሆኑ ስለታወቀ የኤርትራው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ የወሎው ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ በኤሮፕላን መጡ ሌሎችም መምህራንና ሊቃው ንት ከየአውራጃው መጥተው ፍት ሐቱ ሲፈታ ሰንብቶ ሐምሌ ፳፯ ቀን ሬሳው ከሊቀ ጳጳሱ ቤት ወደ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ብቡኑ መቅደሱ ከቀሳብሩ አጠገብ አረፈ ከዚያ በኋላ ለሊቀ ጳጳሳት መጽሐፉ እንደሚያዝዘው ሥርዓቱ ሁሉ በትክክል ይፈጸም ጀመር ።

መዘምራኑ በአንድ ወገን እያሬ ረስ እያደረሱ ስለብፁዕ አቡነ አብ ርሃም ዕረፍት ጥሩ ጥሩ ምሥጢር ያለው ቅኔ እየተቀኙ ሌላውንም የሚገባውን ጸሎት ሁሉ እየጸለዩ ቀሳውስቱም ዲያቆናቱም እስከ ፮ ሰዓት ድረስ የፍትሐቱን ሥርዓት ፈጸሙ ። በ፮ሰዓት ቅዳሴ ገቡና በቅዳሴው ውስጥ ገባሬ ሠናዩ ቄስ የዮሐንስን ወንጌል ምዕ ፲ ካነበቡ በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የወንጌ ሉን ቃል ተርጉመው ለምእመናኑ አስረዱ ነጽር በተባለም ጊዜ ።

መነኰሳት ሬሳውን በወርቅ ማጥን ተሸክመው ዙሪያውን ጳጳ ሳት አጅበው ለሊቀ ጳጳስነታቸው ማዕረግ ተሰጥተውት የነበረውን አርዌ ብርቱንና የወርቅ ወንጌሉን ይዘው የወርቅ ዘውድንና የወርቅ አክሊልን የደፉ አራት ዲያቆናት ይዘው ብቅ ባሉ ጊዜ ሁሉም መን ፈሳዊ ሰላምታ ሰጥቷል ። በዚህ ጊዜ ሦስት ጊዜያት ኡደት ሲደ ረግ መዘምራኑ ወተቀበልዎ ... እያሉ ይዘምሩ ነበር ከኡደት በኋላ ሬሳው ያለበትን ማጥን ከዚያው ከሊቀ ጳጳሱ ግቢ ካለችው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከምድር ቤቱ ውስጥ አስቀድሞ ከተዘጋ ጀው የመቃብር ቤት ከተቀመጠ በኋላ እጨጌው ብፁዕ አቡነ ዮሐ ንስ ለኀዘኑ ለተሰበሰቡት መኳንን ትና መሳፍንት ወይዛዝርት ሹማ ምንትና ሕዝብ ሁሉ የብፁዕነታቸ ውን ደግነትና መንፈሳዊነት እየ ጠቀሱ ኀዘንተኞችን የሚያጽናና ቃለ ምዕዳን ካደረጉ በኋላ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኗል ።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ከላይ እንደተገለጸው የመጀመሪያ ስማ ቸው ይስታ ነበር በኋላ አብርሃም መባላቸው የደግነት ምልክት ነው ብፁዕነታቸው ሹመትን ሳይፈል ጉት እርሱ ይፈልጋቸው ነበር ያል ተሾሙበት ደብር ያልሰበኩበት ሀገር የለም ይባላል ልቡናቸው ብሩህ ከመሆኑ የተነሣ በተወለዱ በ፯ ዓመታቸው መቶ አምሳ ዳዊት ከእነንባቸው ከእነመኃልይ በቃላ ቸው አጥንተዋል በ፲፫ ዓመታ ቸው ቅኔ ስለአወቁ በነጋሪት ላይ ቁመው ተቀኝተዋል፡ ምክንያ ቱም አዕምሯቸው የአዋቂ ቢሆ ንም በቁመት ሕፃን ነበሩና ቅኔ ውን ከተመረጠው ጆሮ ለማድረስ እንዲመቻቸው ነው፡

ማናቸውንም ትምህርት ቢሆን ከሰሙት በኋላ ሳይደገም በአንድ ጊዜ ይይዙት ነበር እስከ ፳፫ ዓመት ድረስ ፬ቱን ጉባኤ አጠኑ ከዚያ በኋላ እየዞሩ ሲሰብኩ ከማ ዕመ ቃላቸው የተነሣ ወይስተሉ በአጽምአቱ እንደተባለው የሚስ ማቸው ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ትምህርታቸውን ለማዳመጥ ይቻ ኩል ነበር መማርና መንፈሳዊ መሆን ለዚህ ይበጃልና ሑሩ ወመ ሐሩ ያለውን የእውነተኛውን መምህር የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ተከትለው ጽድቀ ወንጌልን አስተምረው የትሩፋቱንም ሥራ ሠርተው እግዚአብሔርንና ሰውን አስደስተው ብፁዕ አቡነ አብር ሃም በተወለዱ በ፸ ዓመታቸው ቢያርፉም መልካም ሥራቸው ሕያው ሆኖ ለሁል ጊዜ ይኖ ራል ፡

መልካም ሥራ ሠርቶ ለተከ ታይ ትውልድ ትቶ ማለፍ ከማን



# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጥቅሶች

ከመ·አእ(መክብብ አጥናው)

ሮሜ፡፮—፲፬ ከሕገ ኦሪት ነፃ ወጥ ታችሁ በሐዲሱ የሕገ ወንጌል ጸጋ ሥር የሆናችሁ ሁሉ የኃጢአት ተገዥዎች አትሆኑም ።

## —ሐዲስ ሕይወትን መው ረስ፡

ሕዝቅኤል ፴፮—፳፮—፳፯= ሐዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ ፡ ሐዲስ መንፈስንም በውስጣችሁ አሳድ ራለሁ ፡ እንደ አለት (ድንጋይ) የጠነከረውን ልብ አውጥቼ የለሰ ለሰውን የሥጋ ልብ እሰጣችኋ ለሁ። መንፈሴን በውስጣችሁ አኖ ራለሁ ፡ በሥርዓቴ እንድነት ተመ ላለሱ ትእዛዜንም እንድትጠብቁ አደርጋለሁ ።

፪· ቆሮ· ፭—፲፯= በክርስቶስ ያመነ ሁሉ እርሱ ሐዲስ ፍጥረት ነው እነሆ አሮጌው ሥርዓት አልፎ በቦታው ሐዲስ ሥርዓት ተተክቶአል ።

## በፍጹም እምነትና በንስሐ ሕይወት የሚወረስ ጸጋና በረከት

ማር ፩·፲፭ ጊዜው ስለደረሰ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባ ለችና ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ ። ዮሐ· ፩—፲፪ ለተቀበሉ ትና በስሙ ላመኑበት ሁሉ የእግ ዚአብሔር ልጆች ይሁኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው ።

የሐዋ፡ ፲፮—፴—፴፩= በጌታ ችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰብህም ትድናላ ችሁ።

የሐዋ፡ ፪ ፡ ፴፰—፴፱ ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሠረይላች ኋል። የመንፈስ ቅዱስንም ጸጋ ትቀበላላችሁ ። ይህም ተስፋ ያለው ጸጋና በረከት ሁሉ ለእናን ተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም እግ ዚአብሔር አምላካችን ለሚጠራ ቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ የተሰጠ ነው ።

ኢሳ፡ ፵—፴፰= እግዚአብሔ ርን በመተማመን የሚጠብቁ ሁሉ ግን ኃይላቸው ይታደሳል ፡ እንደንሥርም ሆነው በክንፍ ይወ ጣሉ ፡ ይሮጣሉ አይታክቱም ፡ ይሄዳሉ አይደክሙም ።

ሮሜ ፰—፳፰= እግዚአብ ሔር ለሚወዱትና ፈቃዱን ለሚፈ ጽሙ ሁሉን ነገር ወደ መልካም (ክፉውን ሁሉ ወደ ደግ ሊለውጥ ላቸው) ይችላል ።

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ፡

ዮሐ·፲፬፡ ፲፮—፲፰ ዓለም ሊቀበ ለው ቀርቶ ሊያየውና ሊያውቀ ውም እንኳ የማይችለውን ሌላ አጽናኝ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣ ችሁ ዘንድ እኔ አብን እለምናለሁ። እርሱም በውስጣችሁ አድሮ ስለ ሚኖር እናንተ ታውቁታላችሁ ። ዮሐ· ፫፡፭—፮ ከውሃና ከመን ፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚ አብሔር መንግሥት መግባት አይ ችልም ።

ገላ· ፬—፮ ልጆቹ ስለሆናችሁ እግዚአብሔር የልጁን መንፈስ በልባችሁ አሳድሮአል ።

## መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ክርስቲያኖች ጠባይ መንፈስ ቅዱስ የአማኞች ሕይወት ለመልካም ፍሬ ምግባር የተዘጋጀ እንደሆነ ያደርጋል

ዮሐ፡ ፲፮—፲፫ የዕውነት መን ፈስ በሚመጣ ጊዜ ወደ ዕውነት ሁሉ ይመራችኋል ፡ ወደፊት የሚ ፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ ይገልጥላ ችኋል ።

ገላ ፡ ፭ ፡ ፳፪ = የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ፍቅር የመንፈስ ደስታ ሰላም ፡ ትዕግሥት ደግነት በጎነት እምነት ጭዋነትና ራስን መግዛት ናቸው ፡ እነዚህንም የሚ ቃወም ሕግ የለም ።

## በመንፈስ ቅዱስ እንዴት መጸለይ እንደሚገባንና ምስክርነት ለመስጠት የሚያስችለንን ጥበብም ሁሉ በመስጠት ይረዳናል ፡

የሐዋ· ፩—፰ = የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእናንተ ላይ በሚወ ርድበት ጊዜ ከኢየሩሳሌም ከይሁ ዳና ከሰማርያ በመጀመር እስከ ዓለም ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላ ችሁ ።

ሮሜ ፰· ፲፬ (በእግዚአብሔር) በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ሁሉ እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ።

ሮሜ ፰· ፳፮ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ስለማናውቅ መን ፈስ ቅዱስ ድካማችንን በማወቅ

ናውም ክርስቲያን የሚፈለግ መን ፈሳዊ ግዴታ ስለሆነ መማር ብቻ ሳይሆን እንደ ብፁዕ አብርሃም ጉባኤ አስፋቶ ማስተማር ያስፈል ጋል ።

ከቤተ መጻሕፍት ወመዘክር፡— የተገኘ ታሪክ

ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ



www.ethiopianorthodox.org

አጋዥ ኃይልን ይሰጠናል ።

፪—ጢሞ ፪ ፩—፯ እግዚአብሔር የኃይልን የፍቅርንና ራስን ለመግዛት የሚያስችል መንፈስን እንጂ የፍርሃትን መንፈስ አልሰጠንም ።

## ለክርስቲያናዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ቃል አስፈላጊነት

መዝ·፻፲፱· ፱ = ጐልመሳ መንገዱን በምን ያቀናል?

ቃልህን በመጠበቅ ነው ። ከትእዛዝህ አታርቀኝ

አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ አኖርሁ ።

ማር·፲፪—፳፬ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው የምትሳሳቱት ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ባለማወቃችሁ አይደለምን?

፪· ጢሞ ፫፡ ፲፮—፲፯ በቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኘው ቃል ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው። እርሱም ዕውነትን ለማስተማር ፡ የተሳሳቱትን ለመገሠፅና ስሕተትን ለማረም ይጠቅማል።

ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም እንዲሆንና ማንኛውንም መልካም ሥራ ለመሥራት ዝግጁ ሆኖ እንዲገኝ ነው ።

፩·ጴጥ·፪—፪ ሐዲስ እንደተወለዱ ሕፃናት ንጽሑን ወተት ተመኙ ፡ እርሱም በደኅንነታችሁ እያደጋችሁ የምትሄዱበት ንጹሕ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርት (ቃለ እግዚአብሔር) ነው ።

## የጸሎት አስፈላጊነት ፤

ሉቃ፡ ፲፰ ፩ ሳይታክቱ ዘወትር መጸለይ እንደሚገባ ለማስተማር ይህን ምሳሌ ነገራቸው ።

ፊል፡ ፬·፯ የሚያስፈልጋችሁ ዋና ነገር ምስጋና በተሞላበት ጸሎትና አስተብቁአት እግዚአብሔርን መለመን እንጂ በምንም ዓይነት መጨነቅ አይደለም ።

፩· ዮሐ· ፭—፲፬—፲፭ ማንኛውንም ነገር እንደ እርሱ ፈቃድ ብንለምን እንደሚሰማን (ዕርግጠኞች ነን) እናምናለን

## ክርስቲያናዊ ሥርዓተ ኑሮ በኅብረት ፡ በትምህርተ ወንጌል በጸሎትና በምስክርነት

የሐዋ· ፪—፵፪ ያመኑትም ሁሉ የሐዋርያትን ትምህርት በመስማት በወንድማማችነት አብሮ በመኖር ያገኙትን አብረው በመብላት ለጸሎት ይተጉ ነበር ።

፩ ቆሮ፡ ፲፪—፳፬—፳፯ እግዚአብሔርን የሚያሳፍሩ መስለው የሚታዩትን የአካል ክፍሎች እንኳ የበለጠ ክብር እንዲኖራቸው አድርጐ የአካል ክፍሎችን ሁሉ ክብር እንዲኖራቸው አድርጐ የአካል ክፍሎችን ሁሉ አገጣጥሞአል ፡ ይህንም ያደረገው በአካል ክፍሎች መካከል መለያየት ሳይኖር እርስ በርሳቸው እንዲተሳሰቡ ነው ። (የክርስቲያኖችም ሥርዓተ ኑሮ እንደዚሁ ነው)

ቆላ፡ ፫·፲፮ የክርስቶስ ቃል በእናንተ ሕይወት በሙላት ይኑር ፡ ከእናንተ አንዱ ሌላውን በጥበብ ሁሉ ያስተምር ይምክርም ፡ በመዝሙርና በውዳሴ በመንፈሳዊ ዜማም እግዚአብሔርን በማመስገን ዘምሩ ።

ያዕ·፭፡፲፮ ከሕመማችሁ ሁሉ እንድትፈወሱ በደላችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ ፡ እያንዳንዱም ሰው ለሌላው ወገኑ ይጸልይ ፡ የጻድቅ ሰው ጸሎት ታላቅ ኃይል ነውና ።

## የፈተና አመጣጥና መንፈሳዊ ድልን በመቀዳጀት በአሸናፊነት ለመውጣት የሚያስችል ጥበበ እግዚአብሔር ፡

፩·ቆሮ ፲—፲፫ በማንኛውም ሰው ከሚደርሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም እግዚአብሔር ታማኝ ነው ፡ ስለዚህም ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ፈተና እንዲደርስባችሁ አይፈቅድም በምትፈተኑበትም ጊዜ የትዕግሥትን ኃይልና ከፈተናው መውጣት የምትችሉበትን መንገድ ያዘጋጅላችኋል ።

ያዕ፡ ፩—፲፬ እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው ከዚህም በኋላ ምኞት ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ስታድግ ሞትን ትወልዳለች ።

## የመንፈሳዊ ድል መገኛ ኃይል

ማቴ፡ ፳፮—፵፩ = ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ ።

ሮሜ ፲፪—፲፪ = በተስፋ ደስ ይበላችሁ በመከራም ጊዜ ታገሡ ሁልጊዜ ጸልዩ ፡ አማኞች ወንድሞችን በችግራቸው እርዱ ፡ በእንግድነት የሚመጡትንም ሁሉ ተቀበሉ ።

፩· ጢሞ፡ ፮—፲፩ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ አንተ ግን ከዚህ ሁሉ ነገር በመሸሽ ጽድቅን መንፈሳዊነትን እምነትን ፍቅርን በትዕግሥት መጽናትንና ገርነትን ተከተል



ዕብ፡፪፡፲፰— ክርስቶስ ራሱ በተፈተነ ጊዜ ብዙ መከራን የተቀበለ ስለሆነ የሚፈተኑትን ሁሉ ማዳን ይቻለዋል ።

ያዕ፡ ፬—፯= ለእግዚአብሔር ታዘዙ ራሳችሁን ለርሱ አስገዙ ሰይጣንን ተቃወሙት ፡ እርሱም ከእናንተ ይሸሻል ።

## ክርስቲያናዊ አገልግሎት ፡ —ታዛዥ መሆን እንደሚገባ

— ዮሐ·፲፭ ፡ ፲፬— ትእዛዜን ብትፈጽሙ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ ፡

— ፊል·፪፡፲፬ ማናቸውንም ሥራ በምታከናውኑበት ጊዜ አታጉረምርሙ ፡ በቁጣም አትከራከሩ ይህም የሆነ እንደሆነ በዚህ ጠማማና ሥርዓት አልባ ትውልድ መካከል ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ሆናችሁ እንደ ከዋክብት ለዓለም ሕዝብ ታበራላችሁ ።

—ግብርን ለሚገባው ግብርን ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን ክፈሉ ክብር የሚገባውን አክብሩ ፡ ሊኖርባችሁ የሚገባ ዕዳ እርስ በርሳችሁ መፋቀር ብቻ ነው ሌላውን ሰው የሚወድ ሕግን ሁሉ ፈጸመ ማለት ነው

## ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ

—ማቴ· ፳፪—፴፯—፵= እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ ፡ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ ከሁሉ የሚበልጥ የመጀመሪያው ትእዛዝ ይኸው ነው ፡ ይህንም የሚመስል የዚሁ ተከታይ ሁለተኛ ትእዛዝ "ሰውን ሁሉ እንደራስህ ውደድ የሚለው ነው " የሙሴ ሕግና የነቢያት ትምህርት ሁሉ የተመሠረቱት በነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ ስለ ሆነ ተጠቃለው ይፈጸማሉ ።

— ዮሐ· ፲፫—፴፬ እነሆ እኔ ሐዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ ፡ ብትፋቀሩ የኔ ደቀ መዛሙርት መሆናችሁን ዓለም ሁሉ ያውቃል ።

— ቆሮ ፲፫—፲፫ እንግዲህ ለዘለዓለም ጸንተው የሚኖሩ እነዚህ ሶስት ነገሮች ናቸው ፡

፩ኛ/እምነት

፪ኛ/ተስፋ

፫ኛ/ፍቅር ከነዚህም ሁሉ ፍቅር ይበልጣል ።

—ዮሐ·፫፡፲፰ ልጆች ሆይ ፍቅራችን በተግባር የሚገለጥ ዕውነተኛ ይሁን እንጂ በቃል ብቻ አይሁን ።

— ምዕ × ፲= የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች ተለይተው የሚታወቁበት ይኸው ነው ወንድሙን የማይወድ ሁሉ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም ፡

— ምዕ·፬፡፳ እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ ሐሰተኛ ነው ፡ የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ከሆነ የማያየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወደው ይችላል ።

## የክርስቶስን አዳኝነት መመስከር ፡

—የሐዋ፡፬·፳ ፩=እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመመስከር ዝም ማለት አይቻለንም ።

— ምዕ፡፰·፬— በየሀገሩ የተበተኑትም አማኞች ሁሉ በየደረሱበት ይመሰክሩ ነበር ።

፩·ተሰ፡፪·፬= እግዚአብሔር በአደራ የሰጠንን የወንጌልን ቃል ለመጠበቅ የታመንን ሆነን አገኘናል ፡ ስለዚህም ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንመሰክራለን እንጂ ሰውን ደስ ለማሠኘት የምንናገር አይደለንም ፡

—ማቴ· ፲—፴፪፡፴፫= በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማይ ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ ፡ በሰው ፊት የሚክደኝንም ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማይ አባቴ ፊት እሳፍረዋለሁ ።

(ሉቃስ ፱·፳፮ ተመልከት)

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፲፫ የዞረ)

ኛው ይሆን እያሉ ስለሚያስቡ የሚከተለውን መረጃ በአጭሩ እና ቀርባለን ሄድናክዮስ የሚባል አንድ ሰው በቢታንያ ነበር ለእርሱም ፫ ወንዶች ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት ወንዶቹ አልዓዛር ፡ ስምዖን ፡ ኒቆዲሞስ ሲሆኑ ሴቶቹ ማርያም ፡ ማርታ ይባላሉ ፡

ሄድናክዮስም በቢታንያ በክፍል የተለያዩ ደርብና ምድር ቤት ያለው ታላቅ ሕንፃ መኖሪያ ቤት ነበረው ከዚህም ሌላ በዓለ ፋሲካን በዓለ ሠዊትን በሚያከብርበት ጊዜ የቤት ችግር እንዳይገጥመው በኢየሩሳሌም ዙሪያ የከተማ ቦታ ተመርቶ መጠነኛ ቤት ሠርቶ ይኖር ነበር ሄድናክዮስ በሚሞትበት ጊዜ በቢታንያ ያለውን ቤቱን ለአልዓዛር ለስምዖንና ለኒቆዲሞስ በኢየሩሳሌም ያለውን ለማርያምና ለማርታ ሰጥቷቸው ሞተ—

ከዚህ በኋላ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ከቤታቸው ገብቶ ባዘጋጁለት ማዕድ ላይ በመገኘት ራት ከበሉ በኋላ ካመጡለት ኅብስት አንዱን አንሥቶ ጽዋውንም ባርኮ ለውጦ ነገ ለቤዛ ብዙኃን ሆኖ በመልዕልተ መስቀል የሚሠዋው ሥጋዬ የሚፈሰው ደሜ ይህ ነውና ተቀበሉ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍት
# የሊቀ መንክራት ቡሩክ መዝገቡ
# አጭር የሕይወት ታሪክ ፡

ሊቀ መንክራት ቡሩክ መዝገቡ በሁለት አውላዕሎ አውራጃ በአጽቢ ወረዳ በደብረ ገነት ሥላሴ ከአባታቸው መሪጌታ መዝገቡ ካሣ እና ከእናታቸው ወ/ሮ አበዛ ገ/እየሱስ ግንቦት 23 ቀን 1927 ዓ/ም ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በትውልድ አገራቸው ፊደል ቁጥረው ንባብና ዳዊት ከአባ አብርሃ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፀዋተወ ዜማን ከሊቀ መዘምራን አረጋዊ ፈለቀ እና ከአለቃ መርሐ ጽድቅ እንዲሁም ምዕራፍ ጾመ ድጓ ከታወቁት ስመጥር መምህር ከመልአከ ገነት ደስታ ወልደዮሐንስ ተምረዋል ከመምህር ኃይለሥላሴ ዓምዱ ድጓውን በመከለስ ከመምህርነት ደረጃ ደርሰዋል ። ቀጥሎ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ በሁለተ አውላዕሎ አውራጃ ወንበርታ እንዳይማይሆን ከመምህር ገብረ መድኅን መኮንን ቅኔውን ከእነአገባቡ ካጠናቀቁ በኋላ ከመልአከ ገነት ውቤ ተፈሪ የሐዲሳት ተርጓሜን ተምረዋል ፡ ከዚያው በኋላ አቋቋም ለመማር ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ሂደው ጎንደር ከተማ ከመሪጌታ ይትባረክ እና ከመምህር ክፍሌ የበዓታንና የሳንኳ መረግድና ይትባህልን በሚገባ አጠናቅቀው ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ፡

ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው ድህረ ምረቃም አቋቋምና ዜማ በማስተማር ብዙ ተማሪዎችን አስተምረውና አሠልጥነው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

ከዚያ በኋላ ማስተማሩን ትተው በሀገረ ስብከቱ ፈቃድ በሁለት አውላዕሎ አውራጃ በግብር ሰብሣቢነት ተቀጥረው በማገልገል ላይ እንዳሉ ፡ በዕድገት የሁለት አውላዕሎ አውራጃ የቤተ ክህነት ዋና ጸሐፊ ሆነው በመሥራት ላይ ሳሉ እንደገና በችሎታቸውና በጠባያቸው ተመርጠው በሀገረ ስብከቱ የሂሣብ ሹም በመሆን ተዛውረው ሠርተዋል ፡ ከዚያ ቀጥሎ እስከዕለተሞታቸው ድረስ የክ/ሀገሩ ቤተ ክህነት የትምህርት ክፍል ኃላፊ ሆነው በመሥራት ላይ እያሉ በአደረባቸው ከባድ ሕመም ምክንያት በሐኪም፡ ሲረዱ ቆይተው ምንም ሊሻላቸው ባለመቻሉ መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፺ ዓ/ም ከምሽቱ በ፫ ሰዓት



ሊቀ መንክራት ቡሩክ መዝገቡ እኒህ ነበሩ

በተወለዱ ፶፫ ዓመታቸው አርፈዋል ፡ በነጋታው መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺ ዓ/ም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሀ/ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ የሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች እና በሺ የሚቆጠሩ የመቀሌ ሕዝብ ፡ የስምንቱ አድባራት ክህናት መምህራንና ሊቃውንት በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በክብር ተፈጽሞዋል ።

ሊቀ መንክራት ቡሩክ ቤተ ክርስቲያንን በቅን ያገለገሉ በመሆናቸው መልካም አገልግሎታቸውና ቅን አስተሳሰባቸው ለሌላው አርአያ የሚሆን ነው ቢሆንም ሞት የማይቀር የሰው ዕዳ ስለሆነ ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ለነፍሳቸው ዕረፍተ መንግሥተ ሰማያትን እንዲሰጣቸው ቤተ ክርስቲያናችን ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለች ።

ብሎ ለሐዋርያት ሲሰጣቸው ለሦስቱም ወንድማማቾች የተሰጠው ጸጋ እግዚአብሔር ለማንም አልተሰጠም ።

ስለዚህ ቤተ አልዓዛር ፡ ቤተ, ስምዖን ፡ ጽርሐ ኒቆዲሞስ ተብሎ በሦስት ተከፍሎ ይነገር እንጂ ቤቱ አንድነታቸውን አጽንተው ሳይለያዩ በፍቅርና በሃይማኖት ተመሥርተው የኖሩት ።

ሦስቱ ወንድማማቾች አባታቸው ሄድኖክዮስ የሰጣቸው ያው አንድ ቤት ሲሆን ቤተ አልዓዛር የተባለው የተጠቀሰውም ታሪክ የተገኘው አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል ጸሎተ ሐሙስ በጽርሐ ኒቆዲሞስ በሚል ርእስ ተነሥተው ከአዘጋጁት ጽሑፍ ነው ።

ጠያቂው ሻለቃ ሙሉሸዋ ጋረደ በተሰጠው መልስ እንደሚረኩ በመተማመን መልሳችንን በዚሁ እናጠቃልላለን ።



## ስለ ቅዱስነታቸው የኀዘን መግለጫ

ብፁዕ አባታችን የነፍስ መዳኛን ሲያስተምሩ ፡
በምድራዊው ዓለም ሕዝቡ ደግን ሥራ እንዲሰሩ ፡
ችግረኛውን ፡ ተራቢውን ለማላቀቅ ከችግሩ ፡
ትሩፋትን ለግሰዋል እጃቸውን ሰንዝረዋል በየሀገሩ ።
የሃይማኖት ትምህርት እንዲስፋፋ በየቦታው ፡
በገጠር በከተማ እንዲቋቋም ማስልጠኛው ፡
የሐዋርያትን ሥራ ለሰፊው ሕዝብ አሳውቀው ፡
ነው ያለፉት ለተተኪው አስተላልፈው ፡
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፡
የነፍስ መዳኛን ሲያስተምሩ በየአድባራት ፡
ለተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየቦታው መስፋፋት ፡
በእግራቸው ተጉዘው የተዛባውን ለማቃናት ፡
አደራቸውን ተወጥተው ነው ከዚች ዓለም ያለፉት ።
የወላይታ አውራጃ ሕዝብ የአባታችንን ማለፍ ሲሰማ ምን ብሎ ይሆን ፡
ሕዝቡ ከአለበት ችግር ተላቆ ከሌላው ኗሪ ጋር አንድ እንዲሆን ፡
ብለው ያሰቡ ብፁዕ አባታችን ከዚች ዓለም ሲያልፉ ፡
መቼም አይኖሩ የኀዘን አርጩሜ ያልገረፋቸው ወደ አስከሬናቸው ያልከነፉ ።
አምላካችን ሆይ! የአባታችንን ነፍስ ከእነ ይስሐቅና ያእቆብ አጠገብ አኑር ፡
በምድራዊው ዓለም ሳሉ የነፍስ መዳኛን አስተምረዋል ከዳር እስከ ዳር ።
ከኤዶም ገነት ከሚፈሰው የምንጭ ውሃ እንዲጠጡ ልመናችንን እንገልጥልሃለን ፡
የአምላክ ቸርነቱን ነግረው ነው ያለፉት ከጐናችን ።
ምንም ቢወዷት ይህችን ዓለም ከዘለዓለም ቤታችን አይቀር ፡
ፈጣሪአችን ለእኛ ብሎ በስቃይ ዱላ ሲወገር ፡
ያለሥራው የመረር ፅዋን ሞትን የቀመሰ ፡ ጐኑን የሰጠ ለጦር ፡
አርአያነቱን እንድንከተልና እንድናስተምር ነው ምእመናን በሙሉ የሱ ፍጡር ።
አምላካችን ሆይ ብፁዕ አባታችን ምድራዊ ዓለም በቃኝ ብለው ወደ አንተ ገስግሰዋልና ፡
ልናስቀራቸው አልቻልንም በውስተ ሠረገላ ተሸፍነው በቀስተ ደመና ፡
በክብር ቦታ አሳርፋቸው በምድራዊ ሳሉ ተማዕነዋልና ።
እኛም ቀሪዎቹ በምድራዊ ዓለም ያለን ፡
የሃይማኖትን ምንነት ተረድተን ለወገኖቻችን አስተምረን ፡
እንደ ብፁዕ አባታችን የሐዋርያትን ሥራ ተከትለን
ተዘጋጅተን እንቆይ እስኪያበቃ የምድራዊው ዓለም ኑሮአችን ፡
ጥሪውን እስክንሰማ መንገዳችንን እስክንቀጥል ወደ ፈጣሪአችን ።

ዲያቆን ደጀን መኮንን ደምሴ
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት



www.ethiopianorthodox.org

# አፍና ልብ በአንድ ላይ ይመኑ

በልብ የታሰበው በቃል ይነገራል በቃል የተነገረው ደግሞ በሥራ ላይ ሲውል ግቡን ሊመታ ይችላል በልብ ያልታሰበ ግን በቃል ሊነገር አይችልም ።

ልብና አፍ ተባብረው የሚሠሩት ሥራ ሁሉ መሠረት ያለው ይሆናል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ተዋህዶ በዚህ ዓለም ያስተምርበት በነበረው ጊዜ "ከአፍ የሚወጣ በልብ ይታሰባል ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው ከልብ ክፉ አሳብ መግደል ምንዝርነት ዝሙት መሥረቅ በውሸት መመስከር ስድብ ይወጣልና ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው ። በማለት ተናግሯል ማቴ· ፲፭· ፲፰ የሚታሰበው ነገር ሁሉ ጥሩ መሆን ኢለበት መራራ ዛፍ መራራ ፍሬን ጣፋጭ ዛፍ ጣፋጭ ፍሬን እንደሚያፈራ በአፍ አምኖ በልብ ቢክዱ እንደ ይሁዳ መሆን ነው በልብ አምኖ በአፍ ቢክዱ ደግሞ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ያስቆጥራል ቅ ጴጥሮስ ከክርስቶስ ፲፪ ደቀ መዛሙርት አንዱ መሆኑ የታወቀ ነው ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ ሲያስተምር ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድና ሊቃነ ካህናት ጠልተው ቀንተው ተመቅኝተው ገርፈው ሰቅለው እንደሚገሉት በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ በመነሣት የሰውን ወገን ከፍዳና ከመርገም ነፃ ማውጣቱን አስተማራቸው ፣ በተጨማሪም በአይሁድ እጅ በሚያዝበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ አይሁዳን በመፍራት ጥለውት እንደሚበተኑ ሲገልጽላቸው ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ጴጥሮስ ሁሉም ደቀ መዛሙርት ጥለውህ ቢሸሹና ቢበተኑ ቢክዱህም እኔ ሕይወትህን ሕይወት ሞትህን ሞት አደርጋለሁ እንጂ አልክድህም በማለት ተናገረ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወደፊት የሚሆነው ሁሉ አይሠወረውምና ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜያት እንደሚክደው ለሐዋርያው ለጴጥሮስ ገለጸለት ይህም አልቀረም ጌታችን በተያዘበት ምሽት ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ከልቡ ሳይሆን ከጭንቀቱ የተነሣ ሦስት ጊዜያት ፈጣሪውን ከድቷል በመጨረሻ ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ የሚለውን ቃል አስታውሶ ንስሐ ገብቷል ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሦስት ጊዜ የካደው በአፉ ነው እንጂ በልቡ የሚያምነውና የሚከተለው ክርስቶስን ነበር ይሁን እንጂ በልቡ አምኖ በአፉ መካዱ ከጽድቅ ገብቶ አልተቆጠረለትም የአፉን ክህደት አስወግዶ እንደገና የደኅንነት መንገድን ተከትሎ ከሐዋርያት ጋር አንድ ለመሆን የቻለው ንስሐ ገብቶ ፈጣሪውን ይቅርታ በመጠየቁ ነው በአፍ ክዶ በልብ ቢያምኑ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ መሆን ነው ጴጥሮስን ንስሐው እንጂ የልቡ እምነት አላዳነውምና እንዲሁም ከላይ እንደተጠቀሰው ይሁዳ በልቡ የካደ ቢሆን በአፉ ግን አማኝ ነበር ክርስቶስ ከመረጣቸው ፲፪ ደቀመዛሙርት አንዱ ነበር ለገጸ በረከት ከሚገባው ገንዘብ ከመቶ አሥሩን ለራሱ እያደረገ የቀረውን እንዲያስቀምጥ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር ፣ ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ሴት ዋጋው ፫፻ ብር የሚያወጣ ሽቱ ይዛ መጥታ በጌታችን ራስ ላይ አፈሰሰችው ፣ በዚህ ጊዜ ይሁዳን የቆጨውና የነደደው ከመቶ አሥሩ ሳይከፈለው በመቅረቱ ነበር ይህንን የቀረበትን ገንዘብ ለማሟላት ሲል ክርስቶስን በልቡ ከዳው በአፉ ግን ሰላማዊ ሰው መስሎ ይታይ ነበር።

በዚያን ጊዜ አይሁድ ክርስቶስን ይዘው ገርፈው ሰቅለው ለመግደል የሚፈልጉበት ጊዜ ሲሆን መልኩን አይተውት ስለማያውቁ የሚያስይዛቸው ሰው ይፈልጉ ነበር ፣ ይሁዳ በሽቱው ገንዘብ ሽያጭ የቀረበትን ገንዘብ ለማግኘት ሲል ፴ ብር እንዲሰጡት እርሱም ክርስቶስን ለማስያዝ ከአይሁድ ጋር ተስማማ ።

በመጀመሪያው ሰላሳውን ብር ተቀበለና አይሁድን እየመራ ክርስቶስን ለማስያዝ ወደእርሱ ቀረበ ሰላምታ ሰጥቶ የምስመው የምትፈልጉት ክርስቶስ ስለሆነ እንድትይዙት ብሎ ነገሩን አስረድቶ እርሱ ፊት ለፊት አይሁድ በኋላ በኋላ እየተከታተሉ ሄደው ጌታ ካለበት ሲደርሱ ይሁዳ ሰላማዊ ሰው በመምሰል ሊስመው ሲል ሁሉ የማይሠወረው አምላክ ሰላማዊ መስለህ ልታስይዘኝ መጣህን ለአንተ በግድ የምሰቀልና የምሞት መስሎሃል እኔ ግን የመጣሁት በፈቃዴ ተሰቅየ ሙቼ ተነሥቼ የሰውን ልጅ ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማውጣት ነው በማለት የይሁዳን የልብ ክዳት የአፉን ብቻ ሰላማዊት ገልጾበታል ይህ ሰው በአፉ አምኖ በልቡ ናው በመካዳቱ ከአይሁድ የተቀበለውን ገንዘብ እንኳን ሳይጠቀምበት ሕይወተ ሥጋው ከማለፉ ደርሷል ።

ይህንንም ሐዋርያው ጴጥሮስ "መቶ ሃያ በሚያህሉ ሰዎች ማኅበር አብረው በነበሩ በወንድሞቹ መካከል ተነሥቶ አለ ወንድሞቼ ሆይ ኢየሱስን ለያዙት መሪ ስለ መሆናቸው ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ይገባ ነበር ከእኛ ጋር ተቆጥሮ ነበርና ለዚህም አገልግሎት ታድሎ ነበርና ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩ ሁሉ ታወቀ ስለዚህም ያ መሬት በቋንቋቸው አኬልዳማ ተብሎ ተጠራ እርሱም የደም መሬት ማለት ነው" ይላል የሐ· ሥራ ፩·፲፱

ይህንን ሁሉ ሥቃይ ያደረሰው በአፍ ሰላማዊ መስሎ በልብ መካዳት ነው ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር ፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳሥነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና ፣ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና " ብሏል ሮሜ ፲·፲ ሁላችንም የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን መጠን ክርስቶስን በአፋችንም በልባችንም ለመከተል መጣር ይኖርብናል ተንኮላችን በልባችን ይዘን በአፋችን ደጋጎች መስለን መታየት አይኖርብንም እንዲሁም በልባችን ትክክለኛ የሆነ እምነትን ይዘን በአፋችን እግዚአብሔርን መካድም አይገባንም አፍና ልብ በአንድ ላይ ይመኑ ተብሎ ተጽፎ አለና ።

ሊ·ኅ·ልማነ ወርቅ በዛብህ



# ቅዱስ ዑራኤል

## መራሄ ብርሃናት (የብርሃናት ሁሉ መሪ)

መላእክት ፦ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች
፦ የምስራች አብሳሪዎች ።
፦ የሰው ልጅ ጠባቂዎች ወዘተ· ናቸው ።

መላእክት ዘወትር ሳይሰለቹ ፣ ሳያቋርጡና ሳይደክሙ "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ "ትርጓሜውም" ክብር ለእግዚአብሔር በሰማይ ይሁን ሰላምም በምድር ለሰው በጎ ፈቃድ " እያሉ ልዑል እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ። ከነዚህም ውስጥ ቅዱስ ሁራኤል አንዱ ስለመሆኑ ሄኖክ በመጽሐፉ "ለምስጋና የሚተጉ የከበሩ መላዕክት ስማቸው ይህ ነው ። ከከበሩ ከመላዕክት አንዱ ዑራኤል በመብረቅና በነጎድጓድ የተሾመ ነው? ሲል ገልጾታል መጽሐፈ ሄኖክ ፳፡፩-፪

ከጥቅሱ የምንረዳው ቅዱስ ዑራኤል እግዚአብሔርን ከማመስገን ሌላ መብረቅንና ነጎድጓድን የሚያዝ የብርሃናት ሁሉ መሪ እንደሆነ ጭምር ነው ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ንጉሥ ሄሮድስ ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳይገድልባት ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ ቅዱስ ዑራኤል አብሯት እንደሔደና ዳግመኛ ጌታችንን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ተሰቅሎ ሳለ ለንጊኖስ የተባለው ሰው ቀኝ ጎኑን በጦር ሲወጋው የፈሰሰውን ደምና ውሐ ከመላእክት አንዱ ቅዱስ ዑራኤል በብርሃን ጽዋ ተቀብሎ በዓለም እንደረጨውና በረጨበትም ቦታ ላይ አብያተ ክርስቲያናት እንደታነፁ በድርሳኑ ላይ ተጽፎ ይገኛል ።

ከብዙ ዘመናት በፊት ኢየሩሳሌም በዕብራውያንና በባቢሎናውያን ጦርነት ምድረ በዳ ሁና በጠፋች ጊዜ ዕዝራ ሱቱኤል የተባለ ሰው ነበር ።

ዕዝራ በኢየሩሳሌም ጥፋት አርባ ስድስቱ የኦሪትና የነቢያት መጻሕፍት በተቃጠሉና በተማረኩ ጊዜ በምድረ ራፊድ መሪር የሆነ እንባውን እያፈሰሰ ለፈጣሪው ጸሎት በማድረግ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ።

ዕዝራ ጾሙን ከጨረሰ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ዑራኤል በሰማይ የእሳት ጽዋ ይዞ መጣና እንዲጠጣ አዘዘው ። እዝራም እሳትህን ወደ አፌ እጨምር ዘንድ ከቶ አይቻለኝም አለው። መልአኩ ቅዱስ ዑራኤልም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሆነ ፈጽም ብሎ ሲናገረው እዝራ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የእሳቱን ጽዋ ጠጣ።

እዝራ የእሳቱን ጽዋ በጠጣ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና እግዚአብሔር የተሰወረውን ጥበብ ገለጠለት ። ከአፉ የሚወጣውንም ቃል ይጽፉ ዘንድ ጸሐፊዎች እንዲመጡለት በእጁ አመለከተ ።

ጸሐፊዎችም ከመጡለት በኋላ አርባ ስድስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአገሩ ቋንቋ እሱ እየተናገረ እነሱ እየጻፉ በ፵ ቀን ውስጥ ጨርሰዋል በዚህ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

# የደስታ ዋስትና ምን ይሆን ?

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች የደስታ ዋስትና መልካምን ሥራ ማግኘት ብዙ ገንዘብ ከባንክ ማጠራቀም የተለያዩትንም የእህል አይነቶች መሰብሰብና እንሹራንስንም መግባት ነው ብለው የሚመልሱ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል ።

ግን የደስታ ዋስትና እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በመሰብሰብ ሳይሆን በዘመን ብዛት የማያሻር በጊዜው ሁኔታ የማይለወጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ፍሬ ሰላም ነው ሲል የገለጸው ሰላም ነው ።

ገንዘብ በብዛት ሲሰበሰብ ይጠፋል ይዝጋል ሌባም ይሠርቀዋል እህልም ቢሆን በገፍ ቢሰበሰብ ነቀዝ ይበላዋል ምቀኛም ይዘርፈዋል ፡

ስለዚህ እነዚህ የደስታ ዋስትና ሊሆኑ አይችሉም ።

የደስታ ፍጹም ዋስትና የሚሆነውና ሙሉ በሙሉ የሚታመነው ሰላም ብንል ከእውነት የምንርቅ አይመስለንም ።

በሀገር ውስጥ ሰላም ካለ ሁል ጊዜ ደስታ ነውና ደስተኛና ጤነኛ ሁኖ ለመኖር ይቻላል እያንዳንዱም ሰብአዊ ፍጡር ጤነኛና ደስተኛ ሁኖ ከኖረም ከዚህ የበለጠ የደስታ ዋስትና ስለማይኖር የደስታ ዋስትና ሰላም ነው የምንለው ከዚህ የተነሣ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ሰላም ከጠፋና ሰው ከተፈጥሮ ኀደኛው በዓይነት የሚያይም ከሆነ ጣፋጭ ምግብ እንደ እሬት የሚመር ነጭ ወተት ጠቁሮ እንደ ሚታይ የአደባባይ ምሥጢር አይደለም ። ችግር የለኝም ቤቱም ሙሉ ደስታ የሰፈነበት ነው ለማለት የሚችለው በቤት ሰላም ሲኖር ነው በዓለም ውስጥ ሰላም ተስፋፍቶ ወንድም ከወንድሙ ጋር ሲረዳዳ ዘመድም ከዘመዱ በማንኛውም ነገር ሲተጋገዝ ማየት ፍጹም ደስታ አለ ማለት ይቻላል ።

አለዚያ ግን በአፍ ብቻ ሰላም ሰላም በማለት እጅ ለእጅ እየተጨባበጡ ውስጣዊ ሰላም የሌለውን ሰላምታ ቢለዋወጡ የደስታ ዋስትና አለ ማለት የማየጨበጠውን ነፋስ እንደ መጨበጥ የሚያስቆጥር ነው ።

እርግጥ በእጅ ሰላምታ መለዋወጥ አስፈላጊ አይደልም ማለታችን አይደለም እጅ በእጅ መለዋወጥም አይከፋም ነገር ግን ያ በአፍ የሚነበበው የሰላም መለዋወጥ ከአንገት በላይ ሳይሆን ከልብ የመነጨ መሆን አለበት ማለታችን ነው ።

ከአንገት በላይ ሰላም ሰላም መባል ዋጋ እንደሌለውና ጥቅም እንደማይሰጥ ሲያስገነዝብ ወንጌላዊው ዮሐንስ በአንደኛው መልእክቱ (ደቂቅየ ኢንትፋቀር በቃል ወበልሳን ዘእንበለ በምግባር ወበጽድቅ) ልጆች ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ ብሏል ፩ኛ ዮሐ ፫ ፡ ፲፰።

ወንጌላዊው ዮሐንስ እንደተናገረው እያንዳንዱ ሰው ሰላምን ቢይዝ የሚለዋወጠውም ሰላምታ ከልብ የመነጨ ቢሆን ኑሮ ሰው እርስ በርሱ ባልተጣላም ነበር በየክፍላተ ዓለምም የጦርነት ድምፅ ባልተሰማም ነበር ነገር ግን እርስ በርሱ በዓይነ መዓት የሚተያየውና በጠባብ ሊተላለፍ የማይችለው የደስታ ዋስትና የሆነው ሰላም ከመካከሉ ስለጠፋ ነው ።

ባሁኑ ጊዜ በጋዜጦች በመጽሔቶችና በልዩ ልዩ መሰራጫዎች ስለ ዓለም ስለ ሰው ደኅንነት ጥሪ ሲደረግና የሰላም ንባብ ሲነበብ እንሰማለን ታዲያ ሲነበብ የምንሰማው የሰላም ጥሪ በሥራ ሲተርጐም እናየውም በየዕለቱ ይህን ያህል ሕዝብ አለቀ በዚህ ቀን ይህን ያህል ሕዝብ ቤቱ በሮኬትና በሚሳኤሎች ከተማው ስለ ተመዘበረ መጠጊያ አጣ የሚለውን እንጂ እገሌ በተባለው ሀገር ሰላም ሰፍኖ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲጓዙ አየን ሲባል አንሰማም

(ወደ ገጽ ፲፩ ይዞሯል)

ቃሉን የሚጽፉት ማታ ማታ እራታቸውን ይበሉ ነበር ። እዝራ ግን ፈጽሞ ምግብ አልበላም ነበር ። እዝራ በቅዱስ ዑራኤል እጅ ከአምላክ የተላከለትን ጽዋዐ እሳት ጠጥቶ እውቀት ተገልጾለት የጠፋትን መጻሕፍት ስለመጻፉ ሄኖክ በመጽሐፉ እንዲህ ሲል ገልጾለታል ። "የፍጥረት ሁሉ ገዥ ጌታ በሰማይ በሰራዊት የሾመው መልአኩ ቅዱስ ዑራኤልም በኔ እውቀትን አሳደረብኝ ብሏል ።

በየአመቱም ሐምሌ ፳፪ ቀን የሚከበረው በዓል ዕለቱ የእመቤታችን ይሁን እንጂ ታላቁ መልአክ ቅዱስ ዑራኤል ለዕዝራ ጽዋዐ እሳትን ያጠጣበት ቀን በመሆኑ በስሙ ቤተ ክርስቲያን በታነጸበት ቦታ ሁሉ በዚህ ዕለት በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል ።

ተማሪ ለጋስ ኃይሉ ከቅዱስ ዑራኤል ሰ/ት/ቤት





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 1137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org